አዲስ ዘመን
እናድ
እሁድ 81ኛ ዓመት ቁጥር 212 ሚያዝያ 2 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ

# ከሕዝብ የተነሱ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ስመመለስ እየሠራ መሆኑን የገንዘብ ሚኒስቴር አስታወቀ



ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- በመላው አገሪቱ በተደረጉ ውይይቶች ከሕዝብ የተነሱ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ደረጃ በደረጃ ለመመለስ እየተሠራ መሆኑን የገንዘብ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር እዮብ ተካልኝ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በቅርቡ በተደረጉ ሕዝባዊ ውይይቶች ከኢኮኖሚ ጋር በተያያዘ ከሕዝብ በርካታ ጥያቄዎች ተነስተዋል፡፡ ሕዝቡ ያነሳቸውን ጥያቄዎችም በየደረጃው ለመመለስ መንግሥት ትኩረት አድርጎ እየሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

ከሕዝብ የኑሮ ውድነት፣ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል፣ የውሃና መብራት መሰረተ ልማቶችን ላይ ያሉ ክፍተቶችና አገልግሎት አሰጣጦች ላይ ያተኮሩ ጥያቄዎች ተነስተዋል ያሉት ዶክተር እዮብ፤ በተለይ ከኑሮ ውድነት ጋር በተገናኘ የተነሱ ችግሮች በቶሎ መፈታት እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

የኑሮ ውድነቱን ለመፍታት ከፍተኛ ሥራ ይጠይቃል፤ ይህን ሥራ በየደረጃው ያለው አመራር ሕዝብን አስተባብሮ መሥራት አለበት፡፡ ለምሳሌ ዘይት ላይ የነበረውን እጥረት ለመፍታት ባልተለመደ መልኩ መንግሥት በቀጥታ ገብቶ ግዢ እንዲፈጸም ተደርጓል ብለዋል። በዚህም መሰረት 12 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሊትር ዘይት ወደ አገር ውስጥ

ከሕዝብ የተነሱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## ከሕገወጦች የተያዘው ከ750 ሺህ ሊትር በላይ ዘይት ለሕብረተሰቡ ተከፋፍሏል

- የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ

ገጽ 4

# የአዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ በመሰረተ ልማት ችግር ወደ ኋላ መቅረቱን ገለጸ

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- አዲስ ትውልድ ዩኒቨርሲቲዎችን ለማሳደግ በሚል አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መሰረተ ልማት እንዳያስፋፋ ትኩረት በመነፈጉ ወደ ኋላ መቅረቱን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት ፕሮፌሰር ጣሰው ወልደሃና ገለጹ።

ፕሮፌሰር ጣሰው ወልደሃና ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት 30 ዓመታት አዳዲስ ትውልድ ዩኒቨርሲቲዎችን ለማሳደግ በሚል እሳቤ ዩኒቨርሲቲው ትኩረት በመነፈጉ በቂ መሰረተ ልማት የሌለውና የጤናው ዘርፍ አገልግሎትም በቅሬታ እንዲሞላ ምክንያት ሆኗል።

ከኋላው የተቋቋሙ ዩኒቨርሲቲዎች ከፍተኛ መሰረተ ልማት ሲገነባላቸው በአንጻሩ የአዲስ አበባ ዮኒቨርሲቲ በነበረው እንዲቀጥል መገደዱ ካለው ተማሪ ብዛት፣ ከጥናትና ምርምር ስራዎቹና ከያዘው አገራዊ ተልእኮ አንጻር የሚገባውን ቁመና መላበስ እንደተሳነውም አመልክተዋል።

እንደ አገር ምርምር ለማካሄድና የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማዘመን ሥርዓተ ትምህርት የሚቀዳው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ነው። ሆኖም ዩኒቨርሲቲው ያለው አገራዊ ኃላፊነቱ እየታወቀ ትኩረት በመነፈጉ አጠቃላይ እንቅስቃሴው ላይ ችግር ፈጥሮበታል።

ተቋሙ በመሰረተ ልማት ወደ ኋላ መቅረቱ ሲታወቅ ባለፉት አምስት ዓመታት የተለያዩ ግንባታዎችን እንዲያከናውን ተፈቅዶለት ወደ ስራ ገብቷል። ፒያሳ የሚገኘው የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ክፍልና በዋናው ጊቢ ግንባታዎች የተጀመሩ ቢሆንም በገንዘብ እጥረት ምክንያት ግንባታዎቹን በወቅቱ ማጠናቀቅ አልተቻለም።

ዩኒቨርሲቲው የትኩረት መስኮቹ የጤና እና የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፎች ቢሆኑም የሚያገኘው በጀት ከ400 ሚሊዮን ብር የማይበልጥ ነው። በአንጻሩ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማንኛውንም የሪፈራል ህክምና አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው ብለዋል።

ዩኒቨርሲቲው ትኩረት አድርጎ ይሰራል ተብሎ የሚታሰበው በጤናው ዘርፍ ነው። 20 ሚሊዮን ተገልጋይን ለማዳረስ የታሰበው የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል መሰረተ ልማቱ ተዳክሞ፣ በተረከበው 15 ሄክታር መሬት ግንባታ ለማካሄድ የገንዘብ እጥረት

የአዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፕሮፌሰር ጣሰው ወልደሃና






ዜና

# በኤሌክትሪክ አገልግሎት አሰጣጥ እየተጉላሉ መሆኑን ተገልጋዮች ተናገሩ

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የሚገኙ ነዋሪዎች በኤሌክትሪክ አገልግሎት አሰጣጥ ምክንያት ለእንግልት መዳረጋቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ተናገሩ።

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስምንት ሻወል ደማ ትምህርት ቤት አካባቢ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለሳምንት ያህል ከተቋረጠባቸው አካባቢዎች አንዱ ነው።

የዚሁ አካባቢ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ከድጃ ኑሪ በኤሌክትሪክ መቋረጥ ምክንያት ለሳምንት ያህል በጨለማ ውስጥ መሆናቸውን ተናግረዋል። በነጻ የስልክ ቁጥር 905 ደውለው በማስመዝገብ እንዲሁም ቢሮ ሄደው ያሳወቁ ቢሆንም ምላሽ እንዳላገኙ ይናገራሉ።

ወይዘሮ ከድጃ እንደገለጹት በአካባቢው የኤሌክትሪክ ገመድ በመበጠሱ ምክንያት ኤሌክትሪክ ከመቋረጡም በላይ በአካባቢው ላይ ነዋሪ ላይ የአደጋ ስጋት ተደቅኗል። «የተንጠለጠለው የኤሌክትሪክ ገመድ እየቆየ እሳት እየፈጠረ በመሆኑ በተለይ ማታ ማታ በስጋት ነው የምንተኛው ፤ ልጆቼንም በፍርሃት ሰው ቤት ለመውሰድ ተገድጃለሁ » ብለዋል።

ባለሙያዎች በቦታው ከመጡ በኋላ ቆርጠው ያስቀመጡት የኤሌክትሪክ ገመድ ሌቦች ለመውሰድ ሲንትቱት የአካባቢው ሰው ተሰብስቦ ማስመለሱንና የመንግሥት ንብረት እየተዘረፈ መሆኑም አሳውቀናል ነገር ግን ካቦው አሁንም በሚመለከተው አካል አልተወሰደም ብለዋል።

የችግሩ ተጋሪ አቶ ክፍሎም ዋቅጅራ በበኩላቸው ወርሀዊ ግዴታቸውን በመወጣት ተገቢውን ክፍያ



ወይዘሮ ከድጃ ኑሪ

እየከፈሉ ቢሆንም ለሳምንት ያህል በተቋረጠባቸው የኤሌክትሪክ አገልግሎት የተነሳ መቸገራቸውንና ኅረቤት በማስቸገር ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል።

የአካል ጉዳተኛ የሆኑት አቶ ክፍሎም ነገ ተነገ ወዲያ እየተባለ ሳምንት መቆየቱንና በተለይ የተበጠሰው ኤሌክትሪክ በሰው ሕይወት ላይ አደጋ ከማስከተሉ በፊት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አፋጣኝ መፍትሄ መስጠት እንዳለበበት ተናግረዋል ።

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሦስት ኮካኮላ ጀርባ ቅሬታቸውን ያቀረቡት ወይዘሮ አስካለ ከበደ በበኩላቸው የባልቦላ ቅያሬ ጥያቄ ካቀረቡ አንድ ወር ያለፋቸው ቢሆንም እስካሁን መፍትሄ አላገኙም።

ሌላዋ ቅሬታ አቅራቢ ዘውዴ ቢራቱ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 አካባቢ ነዋሪ ናቸው። ቅሬታ አቅራቢዋ እንደሚናገሩት የኤሌክትሪክ ክፍያ



አቶ ክፍሎም ዋቅጅራ

አልከፈላችሁም በሚል ተሽቀዳድሞ ኤሌክትሪክ ከመቆረጡ በፊት ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ ይገባል። ወርሃዊ ክፍያ 500 ብር ባለመክፈላቸውም የተቆረጠባቸውን ለማስቀጠል 150 ብር ቅጣት ከፍለው እየተጠባበቁ መሆኑን ተናግረዋል።

በጉለሌ ክፍለከተማ ወረዳ አራት ተመሳሳይ ቅሬታቸውን ያቀረቡት አቶ አብነት ነጋ በበኩላቸው በኃይል መጨመር ምክንያት ከፖል ወደ ቆጣሪ የሚሄድ ገመድ በመቋረጡ ሰባት ያህል አባወራዎች በጨለማ ውስጥ መሆናቸውም ገልጸዋል።

በ905 ላይ ተደጋጋሚ ጊዜ ሲደወል በፍጥነት የማይነሳ መሆኑንም በመግለጽ መሰል ችግሮች ሲፈጠሩ አደጋ ከማስከተላቸው በፊት በሚመለከተው አካል ፈጣን ምላሽ እንዲሰጠውና 905 ሲደወል በፍጥነት እንዲነሳ ሲሉም አሳስበዋል።



ወይዘሮ አስካለ ከበደ

የአዲስ አበባ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት አቶ በቀለ ክፍሌ በበኩላቸው ቅሬታ በቀረበባቸው አካባቢዎች ያለው ችግር ተጣርቶ ምላሽ እንደሚሰጥበት ገልጸዋል። በሻዎል ደማ ትምህርት ቤት አካባቢ የኤሌክትሪክ ኔትዎርክ ችግር እንደነበረው በመግለጽ ቦክስ ተቀይሯል ብለዋል።

ተገልጋዮች ኃይል ሲያንስ፣ ትራንስፎርመር ሲቃጠል፣ ቆጣሪ ሲቃጠል ወይም ገመድ ሲበጠስ በግልጽ እና በተገቢው መንገድ በማመልከት ፈጣንና ተገቢውን ምላሽ ማግኘት እንደሚችሉ ጠቁመዋል።

ከደንበኞች በሚሰጡ ጥቆማዎች መሰረት ቅሬታ ቀርቦ ያልተስተካከለ ከሆነና አመራሮች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ በማይወጡ ሲሆን ከማዕከል ኃላፊ ጋር በመነጋገር ተገቢ አስተዳደራዊ የእርምት እርምጃ እንደሚወሰድም አመልክተዋል።

## ገንዘብ ሚኒስቴር መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች ያለምንም የውጭ ምንዛሬ ፈቃድ በቀጥታ እንዲገቡ ወሰነ

አዲስ አበባ፡- የገንዘብ ሚኒስቴር መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦች የሆኑት ዘይት፣ ስንዴ፣ ስኳር፣ የህጻናት ወተት እና ሩዝ ያለምንም የውጭ ምንዛሬ ፍቃድ (በፍራንኮ ቫሉታ) በጉምሩክ ኮሚሽን በኩል በቀጥታ እንዲገቡ ወሰነ፡፡

መንግሥት በአሁኑ ወቅት እየተስተዋለ ያለውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋት እንዲቻል እና በርካታ የውጭ አገር የመኖሪያ ፍቃድ ያላቸው ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ሚና መጫወት እንዲችሉ የፍራንኮ ቫሉታ ፈቃድ በተፋጠነ ሁኔታ እንዲፈቀድላቸው ጥያቄ እያቀረቡ በመሆኑ መወሰኑን ሚኒስቴሩ ገልጿል፡፡

ቀረጥና ታክስን በሚመለከት በገንዘብ ሚኒስቴር በ22/3/2013 ዓ.ም በቁጥር ማአ.30/7/51 በተጻፈው ደብዳቤ መሰረት እንዲፈጸም ፤ አፈጻጸሙን በተመለከተ ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት በኩል ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግበት መወሰኑን ከሚኒስቴሩ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

## ኢንተርፕራይዞችን በማጠናከር ረገድ ክልሎች የኦሮሚያን ተሞክሮ መውሰድ እንደሚገባቸው ተገለጸ

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዳማ፡- ኢንተርፕራይዞችን በማጠናከር ረገድ ክልሎች የኦሮሚያን ተሞክሮ መውሰድ እንደሚገባቸው ተገለጸ፡፡ የኦሮሚያ ክልል ጥቃቅን፤ አነስተኛና መካካለኛ ኢንተርፕራይዞችን ለማበረታታት እየሠራ ያለውን ስራ ሌሎች ክልሎችም ተሞክሮውን በመውሠድ ሊተገብሩት እንደሚገባ የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ዋና ዳይሬክተር አቶ ብሩ ወልዴ አሳሰቡ።

ዳይሬክተሩ በአዳማ ከተማ የተቋሙ የስድስት ወር አፈጻጸም ከትናንት በስቲያ በተገመገመበት ወቅት እንደተናገሩት፤ በአሁኑ ወቅት ለኢንተርፕራይዞች መዳከም ቀዳሚ ምክንያት ከሆኑት መካከል የገበያ ትስስር አለመኖር አንዱ ነው።

በዚህ ረገድ የኦሮሚያ ክልል ኢንተርፕራይዞች እስከ ሃምሳ ሚሊዮን ብር ያመረቱትን ለመንግሥት ተቋማት እንዲያቀርቡ ደንብና መመሪያ በማውጣት እየተገበረ ይገኛል። ክልሉ አጠቃለይ ለዘርፉ በሠጠው ትኩረት ለኢንተርፕራይዞቹ በቢሊዮን የሚገመት ብር የገበያ ትስስርም መፍጠር ችሏል። በዚህም በበርካታ ኢንተርፕራይዞች ተጠቃሚ መሆን ችለዋል።

በመሆኑም ይህንን ተሞክሮ ማስፋፋት ከሌሎቹም ክልሎች የሚጠበቅ ይሆናል። ይህንን ተሞክሮ ማስፋፋት አገር ውስጥ የስራ እድልን ከማስፋፋቱና ልምድ እንዲዳብር ከማድረግ ባለፈ የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ተከትሎ የሚከሰትን የዋጋ ግሽበት ለመቆጣጠርም ይረዳል።

እንደ አገር የውጭ ምንዛሬን ለመጠቀም ቅድሚያ ልንሰጥ የሚገባው በቀላሉ በአገር ውስጥ ምርቶች ልንተካቸው ለማንችላቸው እንደ ነዳጅና መድሃኒት ላሉት ሊሆን ይገባል። ለምሳሌ ኢትዮጵያ ከአፍሪካ





አቶ ብሩ ወልዴ

በቀርከሀ ምርት አንደኛ ብትሆንም በርካታ የቀርከሀ ምርቶች ከውጭ በመግባት ላይ ይገኛሉ ያሉት ዳይሬክተሩ ዛሬም ድረስ በቀላሉ በአገር ውስጥ ሊመረቱ የሚችሉ በርካታ ቁሳቁሶች ከውጭ እየገቡ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በዚህ ረገድ በአገር ደረጃ የተዘጋጁት የግዢ አዋጅ ደንብና መመሪያዎች የአገር ውስጥ ምርቶች ቅድሚያ እንዲያገኙ የሚያበረታቱ ቢሆንም ፤ ተቋማት ለእቃ ግዢ የሚያወጧቸው መሥፈርቶች የአገር ውስጥ አምራቾችን ገና ውድድሩ ውስጥ ሳይገቡ የሚያስወጡ ናቸው። ለዚህ ደግሞ የወጡ የመንግሥት ግዢ አዋጆችና መመሪያዎች በክልልም ሆነ በፌዴራል በአግባቡ አለመተግበራቸው አንዱ የችግሩ ምንጭ መሆኑ ተለይቷል።

በመሆኑም አዲስ አደረጃጀት በተቋሙ እየተተገበረ ሲሆን ጠቃሚ አዋጆች እንዲተገበሩና አላሰሩ ያሉ አዋጆችና ደንቦችም እንዲስተካከሉ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት የሚሠሩ ስራዎች እንደሚኖሩ ዳይሬክተሩ ተጠቁመዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አሸባሪው ሕወሓት ከሰብዓዊነት ይልቅ ለፖለቲካ ትርፍ እየሰራ ነው

ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሃል እንዲሉ፣ አሸባሪው ሕወሓት ራሱ ጦርነት ቀስቃሽ ራሱ አልቃሽ የሆነ ውል አልባ ስብስብ ነው። ይህ ቡድን በራሱ አምባገነንነት ወደጦርነት የገባ፣ ከዚያም ከጦርነቱ መውጫ ሲያጣ ጩኸቱን ለዓለም ማሕበረሰብ በማሰማት በየሜዳው የሚንከባለል፣ ትንሽ ድል ያገኘ ሲመስለው ደግሞ ያዙኝ ልቀቁኝ እያለ የሚፎክር ምንነቱን ለመረዳት የሚከብድና ዓላማ የሌለው የሽብርተኞች ስብስብ ነው። ለሕዝብ ተቆርቋሪ በመምሰል በሕዝብ ላይ ግፍ የሚሰራ ሴረኛም ነው። በተለይ እርዳታንና ጦርነትን የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ በማድረግ እያፈራረቀ ለህልውናው ከመጠቀም አንጻር የረጅም ጊዜ ልምድ ያለው የጥቂት ጥቅመኛ ግለሰቦች ስብስብ ነው። በለጋነት እድሜውም በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ የኖረ ነው፡፡

ድርጅቱ በ1977ዓ.ም ከደርግ ጋር ሲያደርግ በነበረው ጦርነት ልክ እንደ አሁኑ ሕዝብን መያዣ በማድረግ ለረሃብ አጋልጦ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያሳያሉ። በወቅቱ በአገሪቱ ተከስቶ በነበረው ድርቅ የተጎዱ የትግራይ አካባቢዎችን ለመርዳት ወደአካባቢው ተልኮ የነበረውን የርዳታ ስንዴ ጭምር በመሸጥ ለመሳሪያ ግዢ ሲጠቀም እንደነበር ታሪክ ያሳያል፡፡

በአንጻሩ ለሰብአዊነትም ሆነ ለትግራይ ሕዝብ ነጻነት የቆምኩ ድርጅት ነኝ በሚል ሲከራከር ይሰማል። ከስያሜውም ጀምሮ ለትግራይ ሕዝብ ነፃነት የቆመና ለዚያ የሚታገል ድርጅት አድርጎ ራሱን ይገልጻል። ነገር ግን አንድም ጊዜ ለትግራይ ሕዝብ መልካም ነገር ሲሰራ ታይቶ አይታወቅም።

ቀደም ሲል ከደርግ ጋር በነበረው ጦርነት ከ60 ሺህ በላይ የትግራይ ተወላጆች በጦርነቱ ሲቀጠፉ የሴራው ጠንሳሾች ግን ከቁጥር ሳይጎድሉ 17ቱን ዓመታት አሳለፉ። በወቅቱ ሕዝቡ በድርቅ ሲጎዳና በረሃብ አለንጋ ሲቀጠፍም የሕዝቡን እርዳታ እየወሰዱ ለጦርነት ሲያውሉ ነበር። በአንጻሩ በርካታ ህጻናት በረሃብ አለንጋ ሲገረፉ ለነሱ ምናቸውም አልነበረም።

ከውጭ ሆነው ስለነዚህ ዜጎች ችግር በየሚዲያው የሚያለቃቅሱትም ቢሆን አንድም ለትግራይ ሕዝብ የሚጠቅም ስራ ሲሰሩ አልታየም። ሕዝቡ በረሃብና በጦርነት አለንጋ ሲገረፍ እነሱ ውስኪ ሲራጩ ይታያሉ። ልጆቻቸውም ቢሆኑ ከብዙሃኑ የአፍሪካ ወጣቶች የተሻለ ትምህርት እድል ሲያገኙና የተንደላቀቀ ሕይወት ሲመሩ ኖረዋል፣ ዛሬም እየኖሩ ነው፡፡

ሆኖም አብዛኛው ትግራዋይ በረሃብ አለንጋ ሕይወቱን እስከማጣት ደርሷል። በርካቶች ደግሞ ጧሪና ቀባሪ ልጆቻቸውን አጥተው በሜዳ ቀርተዋል። ከፊሎቹም አካላቸውን አጥተው ለዘመናት ለችግር ተዳርገዋል፡፡

አሸባሪው ሕወሓት ከሰላሳ አመት በፊት ወደሥልጣን ሲወጣም ቢሆን በቅድሚያ ያደረገው ነገር ቢኖር እንደማገዶ ሲገለገልባቸው የነበሩትን አብዛኞቹን የትግራይ አርሶአደርና ጎልማሳ የትግራይ ዜጎች ወደጎን በማድረግ ጥቂት ቡድኖች ብቻ በማሰባሰብ ሥልጣንና ገንዘብ ጠቅልሎ መያዝ ነበር። በዚህም እያንዳንዱ የራሱን ቡድን መስመር እየዘረጋ እጅ ለእጅ በመያያዝ አብዛኛውን ሕዝብ የከዳ ነው። በዚህ የተነሳ ለ27 ዓመታት በሥልጣን ላይ በነበሩበት ዘመን እንኳ ከፊሎቹ ጠግበው በቁንጣን እስኪሰቃዩ የሀብት ማማ ላይ ሲንፈላሰሱ፣ አብዛኛው ግን ዳግም ሴፍቲኔት ጠባቂ ከመሆን አልዳነም ነበር። ከዚህም አልፎ ለብዙ ዘመናት አብሮ ከኖረው ጎረቤቱ ጋርም እንዳይገናኝ አፍነው በመያዝና ከሌላው ወንድምና እህቶቹ ጋር በጠላትነት ስሜት እንዲተያይ በማድረግ ለስቃይ ዳርገውታል፡፡

ከዚህ ሁሉ በኋላ በመላ ኢትዮጵያውያን ትግል ከሥልጣን ሲነሳ ዳግም መሸሸጊያ ያደረገው የትግራይን ሕዝብ ነው። በዚህ ጊዜ በተለይ ለብዙ ዓመት ሲሰራበት የነበረውን የትግራይን ሕዝብ ከሌላው ማሕበረሰብ የመነጠል አካሄድ በመጠቀም ከሌላው ሕዝብ ጋር እንዲጋጭ በማድረግ የራሱን ዋሻ ለመስራት ሞክሯል፡፡

ይሁን እንጂ ይህ እምብዛም አልተሳካለትም። የትግራይ ሕዝብ በተለይ ያለምንም ምክንያት ሊያጋጩት የሞከሩት የኢትዮጵያ ሕዝብ ወዳጁና አቃፊው እንጂ ጠላቱ አለመሆኑን ዳግም እያሳየ ነው። በቅርቡ የአማራ ክልል ከትግራይ የተፈናቀሉ ዜጎችን አቅፎ በመያዝና በመንከባከብ ሰብአዊነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ አሳይቷል፡፡

በሌላ በኩል ዛሬም ድረስ ስድስት ወረዳዎችን ይዘውበት የሚገኘው የአፋር ክልል ሕዝብም ቢሆን ለትግራይ ወንድምና እህቶቹ የሚደርሰው እርዳታ በአግባቡ እንዲደርስ በማድረግ ረገድ እያደረገ ያለው አስተዋፅኦ በሕዝቦች መካከል ያለው መስተጋብር በምንም አይነት መንገድ ሊበጠስ የማይችል መሆኑን ያሳየ ነው።

ይህ ሁሉ ሆኖ እያለ ግን ሕወሃት ዛሬም ቢሆን በትግራይ ሕዝብ ጫንቃ እድሜውን ለማራዘም ትግል እያደረገ ነው። በተለይ በእርዳታ ስም በ1977 የሰራውን ታሪካዊ ስህተት ዛሬም በመድገም እርዳታ በአግባቡ ወደትግራይ እንዳይገባ በማድረግ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት እያደረገ የሚገኘው ሴራ የቁልቁለት ጉዞውን ከማፋጠን በዘለለ አንዳችም ፋይዳ እንደማይኖረው ያሳያል፡፡

ዛሬም ቢሆን የቡድኑን እኩይ ጉዞ የሚያውቀው መንግሥት ለዜጎች ህልውና ቅድሚያ በመስጠት የሰብአዊ ድጋፎችን የማድረግ ስራውን አጠናክሮ ቀጥሏል። ይህን ድጋፍ ለማስቀጠልም ከፍተኛ ሥራ እየሰራ ነው። መንግሥት እየወሰደ ላለው ተግባርም በርካቶች በጎ ምላሽ እየሰጡ መሆኑም መንግሥት ለሰብአዊነት ቅድሚያ ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን የሚያረጋግጥና የሚያጠነክረው ነው። አሸባሪው ቡድንም ምንም እንኳን እስካሁን በነበረው አካሄድ ጦርነትን መሰረታዊ አቅጣጫ አድርጎ ቢከተልም፣ ህዝቡ ለከፍተኛ ችግር እንዳይጋለጥ የተዘረጋውን የሰላም እጅ ሊቀበል፣ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ከመጣር ይልቅ ልብ ገዝቶ ለሕዝቡ ሰብዓዊ ድጋፍ እንዲደርስ የበኩሉን ሊወጣ ይገባል፡፡


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# ሰላምን ለማስከበር ከሕዝብ ጋር መተማመንን መፍጠር ግድ ነው

አቤል ገ/ኪዳን

የሰላም ጉዳይ አገራዊ ራስ ምታት ሆኖ ቀጥሏል። በሁሉም አቅጣጫዎች ሰላም ብርቅ ሆኗል። ሰላማዊ ነው የሚባል ክልል በአገሪቱ አለ ለማለት ያስቸግራል። በአሸባሪው ሕወሓት የተነሳ ትግራይ ክልል ጦርነት ውስጥ ከገባ ወደ ሁለተኛ ዓመቱ እየተዳረሰ ነው። አፋር ክልል በሕወሓት ምክንያት ሰላም ካጣ ወራት ተቆጥረዋል። አማራ ክልል በአንድ ጎን ሕወሓት በሌላ ጎን ውስጡ የተሰገሰጉ ወንበዴዎች ሰላም ነስተውታል። ኦሮሚያ ክልል በሸኔ የሽብር ቡድን የተነሳ ኢመደበኛ ጦርነት ውስጥ ነው። ቤኒሻንጉል ፣ ደቡብ ፣ ሶማሌ የየራሳቸው ሰላም እጦት አለባቸው። መዲናችን አዲስ አበባ ራሷ የራሷ የሰላም እጦት መንስኤዎች አሏት። አሁን ላይ በአገሪቱ ዜጎች የሚሞቱበት ነገር ከመብዛቱ የተነሳ ሰርግ እንኳን ሞት የሚያስከትል ጉዳይ ሆኗል። ብስራት ሬዲዮ ሰሞኑን እንደዘገበው በአማራ ክልል በ8 ወር ውስጥ ሰርግ ላይ በተተኮሱ የደስታ ጥይቶች 11 ሰዎች ተገድለዋል፡፡

በዚህ ሰአት ሰላም ለምን ይህን ያህል ራቀን? እንዴትስ ሰላማችንን እንመልስ? የሚሉ ጥያቄዎች የሁሉም ሰው ጥያቄዎች ናቸው። መልሱ ግን ቀላል አይደለም። መንግሥት ሰላም ለማምጣት እንዲህ እና እንዲያ እያረግኩ ነው እያለ ነው። እርምጃ ተወሰደባቸው፣ እጃቸውን ሰጡ፣ መሳሪያቸው ተያዘ የሚባሉ ሃይሎች ቁጥር ብዙ ነው። ነገር ግን እነዚህ እርምጃዎች ተጨባጭ እና መሰረታዊ ለውጥ ማምጣታቸውን ለማወቅ አልተቻለም። እርምጃዎቹም በሕዝብ ዘንድ ሰላም እየሰፈነ ነው፣ ሕግም እየተከበረ ነው የሚል መተማመንን መፍጠር የቻሉ አይመስልም። እንዲያውም በተቃራኒው ሰላም የመመለሻ ቀኗም በዚያ ልክ እራቀ ይመስላል። ምኑጋ ነው የተሳሳትነው ምንስ ብናስተካክል ነው የሰላምን መንገድ መልሰን የምናገኘው የሚለው ጥያቄም ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

ለዛሬ ወደ ሰላም ለመመለስ መደረግ ካለባቸው የመጀመሪያ ነው ሊባል የሚቻለውን ለማንሳት ወደድን። እሱም መተማመን ነው። አሁን ባለን ሁኔታ መተማመን አለ ወይ? ሕዝብ መንግሥት ሰላምን ማምጣት ይችላል ብሎ ያምናል ወይ? የሚለው ጥያቄ ወሳኝ ጥያቄ ነው። ምክንያቱም የሚታዩት ምልክቶች በአንዳንድ የሕብረተሰብ ክፍሎች መንግሥት ሰላምን የማስከበር አቅም ወይም ፍላጎት የለውም የሚል ሃሳብ እንዲሰነዝሩ አድርጓቸዋል። ሰሞኑን ከሕዝብ ጋር የተደረጉ ስብሰባዎች ላይ በስፋት የታየውም ይሄው ነው። እንዲያውም አንድ በማሕበራዊ ሚዲያ ሲዘዋወር የነበረ ቪዲዮ ላይ አንድ ተሳታፊ ሰብሳቢዎቹን የመንግሥት ሹማምንት "ከሶስታችሁ ሁለታችሁ ሸኔ ልትሆኑ ትችላላችሁ" ብሎ ሲናገር ታይቷል፡፡

ከሰውየው ንግግር በበለጠ ያ ቪዲዮ በማሕበራዊ ሚዲያ ላይ የተሸከረከረበት እና ብዙዎች የተጋሩበት መንገድ ሃሳቡ የአንድ ግሰለብ ብቻ ሳይሆን የብዙሃን እንደሆነ አመላካች ነው። ሕብረተሰቡ አሁን ከአሸባሪዎች ባልተናነሰ መንግሥትን እና ሹማምንቱን እየተጠራጠረ ነው ማለት ነው። ይህን ነገር አሳሳቢ የሚያደርገው ደግሞ ሰላምን ማስከበር የማንኛውም መንግሥት የመጀመሪያው መሰረታዊ ግዴታ ከመሆኑ አንጻር ነው። መንግሥት ይህን መሰረታዊ ተልእኮውን ለመወጣት አቅም አጥሮታል ወይም ዳተኝነት አሳይቷል የሚል እሳቤ ሲኖር ደግሞ ለብዙ አደገኛ አካሄዶች መወለድ ምክንያት ይሆናል፡፡

መንግሥት ሰላምን ለማስከበር ዳተኛ ሆኗል ወይም አቅቶታል የሚል እሳቤ ሲኖርና ዜጎች ሰላማቸውን ማስከበር የራሳቸው ግዴታ አድርገው ከወሰዱ ሌላ አዲስ እና በጣም አደገኛ ችግር ይፈጠራል። ይሄ በየክልሎች የተደራጁ ልዩ ኃይሎች የፈጠሩትን አቅም ተከትሎ የሆነብንን እንድናስብ ያደርገናል። አሁንም ከመከላከያም፣ ከብሄራዊ ደህንነት ፣ ከፌዴራል ፖሊስ ፣ ከክልል ፖሊስ ፣ ከክልል ልዩ ሃይል ያለፈ በክልል ደረጃ ሌሎች የወጣቶች አደረጃጀቶችን እየፈጠሩ ነው። ይህ አይነት አደረጃጀትና ታጣቂ ሃይል ሲበዛ አገር ይጠቅማል አይጠቅምም ወደፊት የሚታይ ነው፡፡

እንግዲህ ክልሎች በዚህ መልኩ ሰላምን ማስከበር የራሳቸው ሃላፊነት አድርገው አዳዲስ አደረጃጀት እየፈጠሩ ሌላ አላስፈላጊ የፖለቲካ ሙቀት ከጨመሩ፣ ተራው ዜጋ የራሴን ሰላም ማስከበር የራሴ ሃላፊነት ነው ብሎ መንቀሳቀስ ሲጀምር ደግሞ ምን ያህል ችግር እንደሚፈጠር መገመት አያቅትም። ስለዚህም መንግሥት ሰላም ለማስከበር እና የዜጎችን ደህንነት ለማስጠበቅ ብቁ እና ቁርጠኛ እንደሆነ ማሳመን አለበት፡፡

እዚህ ጋር ለያይተን ልናየው የሚገባ ነገር ቁርጠኝነት እና ብቃትን ነው። መንግሥት ሰላምን ለማስከበር የአቅም እጥረት የለበትም በሚለው ላይ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚስማማ ይመስላል። የብዙ ሰው ጥያቄ እና ቅሬታም መንግሥት አቅም ሳያንሰው ነገር ግን ጸረ ሰላም ሃይሎችን ለመቅጣት እና ሰላምን ለማስከበር ዳተኛ ሆኗል የሚል ነው። በእርግጥም አገሪቷ የአሸባሪዎች ሁሉ ቁንጮ እና ሁሉን መጋቢ የሆነውን ሕወሓትን አደብ ማስገዛት የቻለ የጸጥታ ሀይል አላት። ከአገርም አልፎ በአህጉር ደረጃ ሰላም ማስከበር የቻለ ሰራዊትም የኛ ነው። ታዲያ ዋናውን አሸባሪ ወደ ሳጥኑ መመለስ የቻለው መንግሥት ደቃቅቹን አሸባሪዎች መቅጣት አቅቶት ነው? ወይስ እነዚህ ሃይሎች ከአመት በፊት በከፍተኛ ድምጽ አሸንፎ ሥልጣን ለመያዝ ከበቃው መንግሥት የበለጠ ሕዝባዊ ድጋፍ ኖሯቸው ነው? ወይንስ አንዳንዶች እንደሚሰጉት የመንግሥት መዋቅር ራሱ ተጠልፎ ነው? ለነዚህ ጥያቄዎች ብዙ ፖለቲካዊ እና ወታደራዊ ማብራሪያዎች ከመንግሥት በኩል እንደሚሰጡ እርግጥ ነው። ነገር ግን ማብራሪያዎቹ ምንም ያህል አሳማኝ ቢሆኑ እንኳ አሁን በመንግሥት እና በሕዝብ መሀከል በሰላም ዙሪያ ያለው መተማመን ካልተሻሻለ ሰላምን ማስከበር አይቻልም፡፡

መተማመኑ አስፈለጊ የሚሆነው በዋነኝነት ሰላምን ማስከበር የሕዝብ እና የመንግሥት የጋራ ስራ ውጤት ስለሆነ ነው። ሁለቱ እንደ ቀኝ እጅ እና ግራ እጅ ናቸው። የጸረሰላም ሃይሎችን ጉሮሮ አንቆ ትንፋሻቸውን ለማቋረጥ ሁለቱም እጆች መተጋገዝ አለባቸው። ለጊዜው ግን ቀኝ እጅ ግራ እጅን እያመነው አይመስልም። ስለዚህም ግራ እጅ ሆን ብሎ እየለገመ እንዳልሆነ ለቀኝ እጅ ማሳመን አለበት። መንግሥት እና ሕዝብ ካልተማመኑ ክልሎች ሊተማመኑ አይችሉም። መንግሥት እና ሕዝብ ካልተማመኑ የፌዴራሉ የጸጥታ መዋቅር እና የክልሎች የጸጥታ መዋቅር ሊተማመኑ አይችሉም። መንግሥት እና ሕዝብ ካልተማመኑ የላይኛው መዋቅር እና የታችኛው መዋቅር ሊናበቡ አይችሉም። ስለዚህም መንግሥት ሰላም ለማስፈን ቁርጠኛ መሆኑን በተግባር ሊያሳይ እና በሕዝብ ዘንድ አመኔታን ሊፈጥር ይገባል፡፡

ሕዝብ አሁን የደህንነት መስሪያ ቤቱ የማይታዩትን የአገር ጠላቶች ካሉበት ጉድጓድ ጎትቶ ሲያወጣ ማየት ይፈልጋል። ሕዝብ መከላከያ ሰራዊቱ አሁንም ቢሆን የአገር ሉአላዊነትን ለማስከበር ዝግጁ እና ብቁ አንደሆነ ማወቅ ይፈልጋል። ሕዝብ የፌዴራል ፖሊስ በየስርቻው በታጠቁ ወሮበሎች ሲገድል ሳይሆን የክልሎችን ድንበር አቆራርጦ እየሄደ የሽብር ቁንጮዎችን ሲቆጣጠር መመልከት ይፈልጋል። ሕዝብ አሁን አንዱ ክልል ሌላውን በስጋት ሲያይ ሳይሆን በጋራ ተባብረው ሲሰሩ ማየት ይፈልጋል። ሕዝብ የክልል ፖሊስ እና ልዩ ሃይል የፖለቲካ መሳሪያ ሳይሆን የሰላም ዘብ ሆነው መመልከትን ይጠብቃል። በጥቅሉ ሕዝብ መንግሥት በመሰረታዊነት የሰላም ማስጠበቅ ስራውን መስራት እንደሚችል እንዲያሳየው ይፈልጋል። መንግሥት ደግሞ ይህን በማሳየት እምነትን መፍጠር ይጠበቅበታል፡፡

ዜና

# ከሕገወጦች የተያዘው ከ750 ሺህ ሊትር በላይ ዘይት ለሕብረተሰቡ ተከፋፍሏል

- የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ

ዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- በከተማዋ በተለያዩ ጊዜያት በተደረገ የቁጥጥር ስራ ከሕገወጦች የተያዘው ከ 750 ሺህ ሊትር በላይ ዘይት ለሕብረተሰቡ መከፋፈሉን የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ አስታወቀ። ቢሮው የዘይት አቅርቦት ማነስና የዋጋ መጨመር ችግሮችን በፍጥነት ለመፍታት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመስራት ላይ እንደሚገኝም አሳውቋል።

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ኃላፊ አቶ አደም ኑሪ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ቢሯቸው በተለያዩ ጊዜያት ባደረገው የቁጥጥር ስራ ከሕገወጦች የያዘውን ከ750 ሺህ ሊትር በላይ ዘይት ለሕብረተሰቡ ማከፋፈል ችሏል። ሕገወጥ ነጋዴዎቹ ዘይቱ የተወረሰባቸው ገበያው እየፈለገው በሚፈለው ፍጥነት ወደ ገበያ ባለማቅረባቸውና የዘይት ምርቱ አዲስ አበባ ከተማ ገበያ መቅረብ እያለበት ወደ ተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ሲጭኑ በመገኘታቸው ነው።



የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ኃላፊ አቶ አደም ኑሪ

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮም ዘይቱን ከነጋዴዎቹ በመውሰድ ለሸማች ሕብረት ስራ ማሕበራት ማስረከቡን አመልክተው፤ ማሕበራቱ ዘይቱን ለሕብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ ማከፋፈላቸውንም አቶ አደም ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ በቅርቡ የተከሰተውን የዘይት አቅርቦት ማነስና የዋጋ መጨመር ችግሮችን በፍጥነት ለመፍታትም ጥረት ማድረጉን ገልጸው፤ ቢሮው ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና ከዘይት አቅራቢዎች ጋር በመቀናጀት ምርቱ በፍጥትና በተመጣጣኝ ዋጋ በሸማች ሕብረት ስራ ማሕበራት በኩል ለሕብረተሰቡ እየቀረበ እንደሚገኝም አቶ አደም ገልጸዋል።

እንደ አቶ አደም ገለፃ፤ ቢሮው ገበያውን የማረጋጋት ሃላፊነቱን በመወጣት ላይ ይገኛል። ከከተማ እስከ ወረዳ ድረስ በሕግ ማስከበርና በአቅርቦት ክትትል ላይ የሚሰሩ ተቋማት የተወከሉበት ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ስራ ገብቷል። ኮሚቴውም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ የሚመራ ነው።

ኮሚቴው የመጣው ዘይትና ስኳር እንዲሁም ሌሎች ምርቶች በትክክል ለሕብረተሰብ መድረሳቸውን እንዲሁም ለሕገወጥ ተግባራት ተጋላጭ እንዳይሆኑ የማድረግ ተግባርን እንደሚያከናውን አስታውቀው፤የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ በአገር ውስጥ ፋብሪካዎች አማካኝነት የሚመረት ዘይትን እንዲሁም ከውጭም የሚገባውን ወደ ሕብረተሰቡ እንዲደርስ ስራዎቹን በትኩረት እንደሚሰራ አስረድተዋል።

የኮሚቴው ዋንኛ ተግባር ሕግ የማስከበር እንዲሁም አቅርቦት ችግር እንዳይከሰት መቆጣጠር ነው ያሉት አቶ አደም፤ የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ መሰል የሕግ ማስከበር ተግባራትን እንደሚቀጥልም ዋና ኃላፊው አቶ አደም ኑሪ ገልጸዋል።

# "ለጋሽ አገራት ለኢትዮጵያ የሚያደርጉትን ሰብዓዊ ድጋፍ በእጥፍ መጨመር አለባቸው"

- የዓለም የምግብ ፕሮግራም

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ እርዳታ የሚሹ ሰዎች ቁጥር በመጨመሩ ለጋሽ አገራት የሚያደርጉትን የሰብዓዊ ድጋፍ በእጥፍ እንዲያሳድጉ የዓለም የምግብ ፕሮግራም ጥሪ አቀረበ።

የድርጅቱ የኢትዮጵያ ዳይሬክተር ተወካይ ሜተክ ማጅ ከኢዜአ ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ በሰሜን ኢትዮጵያ በነበረው ጦርነት እና በኦሮሚያና ሶማሌ ክልሎች የተከሰተውን ድርቅ ተከትሎ በርካታ ሰዎች የሰብዓዊ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ገልጸዋል።

በጦርነቱና በድርቁ ተጎጂ የሆኑ ከ11 ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያን እና ከ700 ሺህ በላይ የተለያዩ አገራት ስደተኞች አሁን ላይ የለጋሾችን አስቸኳይ ድጋፍ ይፈልጋሉ ብለዋል።

የዓለም የምግብ ፕሮግራም ለእነዚህ ተጎጂዎች የሰብዓዊ ድጋፍ ለማድረስ ከ600 ሚሊዮን ዶላር በላይ ያስፈልገዋል ሲሉም ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች የሰብዊ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ዜጎች ቁጥር ከፍተኛ መሆኑን በማንሳት፤ እስከ ፈረንጆቹ ዓመት መጨረሻ ድረስ የሰብአዊ እርዳታ የሚፈልጉ ተጎጂዎች ቁጥር በትንሹ 20 ሚሊዮን እንደሚሆን ይገመታል ብለዋል።

ለተጎጂዎቹ የሚያስፈልገው ሰብዓዊ እርዳታ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር በእጥፍ መጨመሩን ጠቅሰው ለጋሽ አገራት ለኢትዮጵያ የሚያደርጉትን ሰብዓዊ እርዳታ በእጥፍ እንዲጨምሩ ጥሪ አቅርበዋል።

የተረጂዎች ቁጥር በማሻቀቡ ምክንያት የዓለም የምግብ ፕሮግራም በሶማሌ ክልል ለእያንዳንዱ ተረጂ ሲሰጥ የነበረውን የ15 ኪሎ ግራም ወርሃዊ የጥራጥሬ ድጋፍ ወደ 12 ኪሎ ግራም መቀነሱን ጠቅሰዋል።

ላለፉት ሦስት ተከታታይ ወራት ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ ስደተኞች የሚሰጠው የምግብ ድጎማ ከ18 በመቶ ወደ 16 በመቶ መቀነሱንም በማከል።

ድርጅቱ በአማራ፣ አፋርና ትግራይ ክልሎች ለ3 ነጥብ 4 ሚሊዮን ሰዎች አስቸኳይ የሰብዓዊ ድጋፎችን እያደረገ መሆኑንም ተናግረዋል።



ሜተክ ማጅ

በተመሳሳይ በሶማሌ ክልል ለሶስት ተከታታይ የዝናብ ወቅቶች ባጋጠመው ድርቅ 3 ነጥብ 3 ሚሊዮን ዜጎች ተጎጂ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ከነዚህ ውስጥ ላለፉት ወራት ለ2 ነጥብ 4 ሚሊዮን ተጎጂዎች ድጋፍ ማድረጉን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት በትግራይ ክልል የሰብዓዊ ድጋፍን ለማጠናከር የወሰደው የግጭት ማቆም ውሳኔንም አድንቀዋል። የአገር ውስጥ ግብረሰናይ ድርጅቶች፣ የእርዳታ ሰራተኞችና የሰብዓዊ መብት ተቆርቋሪዎች ውሳኔውን በመልካም እንደተቀበሉትም ጠቅሰዋል።

ከግጭት ማቆም ውሳኔ በኋላ የሰብዓዊ እርዳታ የጫኑ 20 ተሽከርካሪዎችና አንድ ነዳጅ የጫነ ቦቴ ትግራይ ክልል መግባታቸውን ተናግረዋል። ሌሎች ተጨማሪ 35 ተሽከርካሪዎችም የአፋር ክልል ሰሜናዊ ምዕራብ ጫፍ መድረሳቸውን አረጋግጠዋል።

የዓለም የምግብ ፕሮግራም በጦርነቱ በተጎዱ የአማራና የአፋር ክልል ዞኖች ውስጥ ባደረገው የምግብ ዋስትና ዳሰሳ በአካባቢው ከሚኖሩት 98 በመቶ ያህሉ ለከፋ የምግብ ዋስትና ችግር መዳረጋቸውን አረጋግጠናል ብለዋል።

# የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ተግዳሮት እንደተፈጠረበትም ተናግረዋል። 20ሚሊዮን ዶላር የሚጠይቀው ይህ ማዕከል በአፍሪካ ትልቁ የህክምና ቱሪዝም ኮምፕሌክስ እንደሚሆን ጠቁመዋል።

በበጀት እጥረቱ ምክንያት ሆስፒታሉ በርካታ መድሃኒቶችና የህክምና መሳሪያዎች የሉትም። ነገር ግን በሕግ ማስከበር ዘመቻው እንኳን የተጎዱ ወታደሮችን አርተፊሻል እግር ሲገጥም መቆየቱን ተናግረዋል።

እንደ ፕሮፌሰር ጣሰው ገለጻ ጤና ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ በመገንዘብ ዩኒቨርሲቲው ከበጀቱ 50 በመቶው የሚደርሰውን ለሆስፒታሉ ይመድባል። ይህ በቂ ባለመሆኑ በአገልግሎት አሰጣጡ በየጊዜው ሮሮ ይሰማበታል። መንግሥት የጤና በጀት አይመድብለትም። የመድሃኒት እና የህክምና መሳሪያ በበጀት እጥረት የሚፈጠር ነው።

በተለይ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች በርካታ ተገልጋዮች አሉት። በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ሁሉም የመንግሥት ሆስፒታሎችንም የሚያክሙት የጥቁር አንበሳ ሪፈራል ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ዶክተሮች በመሆናቸው መንግሥት ጳውሎስ ላይ ያደረገውን ኢንቨስትመንት ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቢያደርግ ለኢትዮጵያ ትልቅ ውለታ ይውል እንደነበርም ተናግረዋል።

ባለፉት 30 ዓመታት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመሰረተ ልማት የሚሰጠው ሀብት ሲከፋፈል ፍትሃዊ አልነበረም። የዩኒቨርሲቲዎችን አቅም፣ የሕብረሰቡን ፍላጎት፣ የበለጠ ጥቅም ሊሰጥ የሚችልበት የትኩረት መስክ የሚታይበት አሰራር አልነበረም። አሁንም ትኩረት አልተሰጠውም።

የፕላንና ልማት ሚኒስቴር በጉዳዩ ላይ ትኩረት ወስዶ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመሰረተ ልማት ግንባታ ግልጽ በሆነ መስፈርት፣ ተልዕኮ ላይ የተመሰረተና አዋጭነቱ ታይቶ እንዲተገበር ስራዎች መጀመራቸውን አስታውሰው፤ ትግበራው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ተጠቃሚ እንደሚያደርገው ተስፋ አለን ብለዋል።

# ከሕዝብ የተነሱ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

መግባቱንና በየወሩ የ50 ሚሊዮን ሊትር ዘይት ግዢ ለመፈጸም ውሳኔ ተወስኖ እየተሰራ መሆኑን አስታውቀዋል። ይህም በተወሰነ ደረጃ የጠፋውን የዘይት ምርት የማረጋጋት ዕድል እንዳለው ተናግረዋል። ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተያዘው አቅጣጫም በዓለም አቀፍ ደረጃ ችግር ሲፈጠር አገራዊ ችግሩን ለማቃለል ትልቅ ሚና መጫወቱን ያስታወሱት ሚኒስተር ዴኤታው፤ ከበጋ ምርት ብቻ እስከ 24 ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ ምርት እንደሚጠበቅ አስታውቀዋል። ይህ የስንዴ ምርት ከዚህ በፊት የነበረውን አጠቃላይ የፍላጎትና አቅርቦት ክፍተት መሙላት ያስችላል ሲሉም አስታውቀዋል።

በዩክሬንና በራሽያ ጦርነት ምክንያት በዓለም ላይ የምግብ እህሎች ዋጋ ከፍተኛ ጭማሪ ማሳየቱን አስገንዝበው በጦርነቱ የተፈጠረው ዓለም አቀፍ ጫና በቀጥታ ሕዝቡ ላይ እንዳያርፍ መንግሥት ጥረት እያደረገ ነው ብለዋል። ጫናውን ለመቋቋም መንግሥት በተለይ ምርታማነት ማሳደግ ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራ ይገኛል።

በተጨማሪም አትክልትና ፍራፍሬ በየአካባቢው በማምረት መሬት ጦሙን እንዳያድር ማድረግ ይቻላል። ስለሆነም ከሌላ አካባቢ የሚመጣን አትክልትና ፍራፍሬን በመጠበቅ የሚፈጠር እጥረት ተገቢነት የለውም ብለዋል፡፡ በተገኘው ክፍት ቦታ ሁሉ በምግብ ራስን ለመቻል የሚረዱ ምርቶችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። በቀጣይም ሕዝቡ በተደራጀ መንገድ በይበልጥ ወደ ሥራ እንዲገባ ማስተባበርና ማስተማር አንዱ አቅጣጫ ሆኖ ተግባራዊ ይደረጋል ሲሉ ገልጸዋል፡፡ በየአካባቢው ላሉ ችግሮች አካባቢያዊ መፍትሔ መስጠት ቁልፍ መፍትሔ መሆኑን ያስታወቁት ዶክተር እዮብ፤ በከፍተኛ ዋጋ ከውጭ የምናስገባቸውን ምርቶች በአገር ውስጥ የመተካት ሥራ በሰፊው እየተገባበት መሆኑን አስታውቀዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በምግብ ሸቀጦች ላይ የሚታየውን የዋጋ ንረት ለማስተካከል የገንዘብ ሚኒስቴር መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦች የሆኑት ዘይት፣ ስንዴ፣ ስኳር፣ የህጻናት ወተት እና ሩዝ ያለምንም የውጭ ምንዛሬ ፍቃድ (በፍራንኮ ቫሉታ) በጉምሩክ ኮሚሽን በኩል በቀጥታ እንዲገቡ መወሰኑ ይታወሳል፡፡

ፖስቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

## የሀሳብ ዥዋዥዌ...!?

**በየደረጃው ያለ ስግብግብና አልጠግብ ባይ ነጋዴም ዛሬ መሠረታዊ ሸቀጥ እየደበቀና እጥረት እየፈጠረ የሚያጋብሰውን ሀብት ነገ ሲበላው፤ ልጆቹን አስተምሮ ለወግ ለማዕረግ ማብቃት የሚችለው አገር ሰላም ሲሆን ነውና ቆም ብሎ ሊያስብ ይገባል። በሰሞነኛው አንድ መድረክ እንደተገለጸው እሱ እየበላ ጎረቤቱ እየተራበ ሊቀጥል አይችልም። ሲብስበት በሩን ሰብሮ ይገባለታል። በሕዝብ ረሀብና ችግር እያተረፈ ያለው ደላላም ቆም ብሎ ሊያስብና ወደ ህሊናው ሊመለስ ይገባል። በእርግጥ ህሊና ካለው**

አንዳንድ ነገር በባህሪው እዚህና እዚያ መርገጥን፤ አንስቶ መጣልን፤ በሀሳብ መብሰልሰልን፣ መባዘንንና መቅበዝበዝን፤ ማለቂያ የሌለው የሀሳብ ድር ማዳወርን፤ ከፍ ሲልም የሀሳብ ዥዋዥዌ መጫወትን ግድ ይላል። በአገራችን እየተስተዋለ ያለውን አሳሳቢ የኑሮ ውድነት ባሰብሁ ቁጥር እየተፈጠረብኝ ያለው ስሜት እንዲህ ያለ ነው። ውሉ የጠፋና መቋጫ የሌለው የሀሳብ አዙሪት። እናም እንደ አገር፣ መሪና ዜጋ ካሉብን ስር የሰደዱ ፈተናዎች ለዛሬ አምስቱን መነሻ አድርጌ ሀሳብ እቀብላለሁ፤ "እስጥ አገባ፤" እላለሁ፤ ትዝብት አጋራለሁ፤ አጀንዳ አነብራለሁ፤ ሰሞነኛ ገጠመኝን በማሳያነት አቀርባለሁ።

የመጀመሪያው ችግሮች ከመከሰታቸውና ከመባባሳቸው በፊት አነፍንፎ አበክሮ የመከላከል ልምሻ ሲሆን፤ ሁለተኛው ችግሮች ከተከሰቱ በኋላም ቢሆን መንስኤዎቻቸውን አብጠርጥሮ ከመፈተሽ ይልቅ አለባብሶና ሸፋፍኖ የማለፍ አባዜ ነው። ሶስተኛው ደግሞ ችግሮችን ውጫዊ የማድረግ እርግማን ነው። አራተኛው ውጤት ወይም ድል ሲገኝ ደግሞ የመሻማት ክፉ አመል አለብን። አምስተኛው የችግር አረንቋ ውስጥ ተዘፍቀን አንገታችን ላይ እስኪደርስ ያለመንቃትና የማቅለል ክፉ አባዜ ምርኮኛ መሆናችን ነው።

እዚህ ላይ ልብ መባል ያለበት አብይ ጉዳይ ባለፉት ሰባት ወይም አራት አመታት እንደ አገር፣ መሪና ትውልድ የገጠሙን ፈተናዎች፣ ቀውሶችና ተግዳሮቶች ቢያንስ ላለፉት 100 አመታት ሲንከባለሉ የመጡና በእዳ የወረስናቸው መሆናቸው በደንብ ሊጤኑ ይገባል። ስለሆነም የማነሳቸው ችግሮች በአቅማችን ልንፈታቸው እየቻልን ያልፈታናቸውን፤ የሚያስከትሉትን ጉዳት ሙሉ በሙሉ ማስቀረት ባንችል እንኳ መቀነስ እየቻልን በዳተኝነት ወይም በእንዝህላልነት ያልቀነስናቸውን፤ የማድረግ ወይም የመፈጸም አቅማችንን አሟጠን መጠቀም ባለመቻላችን የተባባሱ ችግሮችን መነሻ በማድረግ እንደምሰናዘር ልብ ይሏል ።

በ2013 ዓ.ም ነሐሴ ወር መጨረሻ ላይ፤ የዋጋ ግሽበቱና የኑሮ ውድነቱ ከኢኮኖሚያዊ ችግርነት አልፎ የሰላም፣ የደህንነት፣ የጸጥታና የህልውና ችግር የመሆን ዕምቅ አደጋ የደቀነ ስለሆነ ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኝና አጀንዳ እንዲሆን አገር አቀፍ ውይይት እንዲካሄድ በዚህ ጹሑፍ አዘጋጅና "የኢትዮጵያ ሸማቾች መብት ተቆርቋሪ ድርጅት፤" መስራችና ዋና ስራ አስኪያጅ የመነሻ ሀሳብ(ፕሮፖዛል) መዘጋጀቱንና የጠቅላይ ሚኒስቴሩ የፕሬስ ሴክሬታሪያት በየወሩ በሚያዘጋጀው "አዲስ ወግ" አገር አቀፍ መወያያ ርዕስ እንዲሆን ማሰቡን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፍተኛ የኢኮኖሚ አማካሪ በስልክ አወያይቷቸው ነበር፡፡ በወቅቱም "ችግሩ የምርት ዕጥረት ነው። ምርትንና ምርታማነትን ለማሳደግ መስራት እንጂ ስብሰባ መፍትሔ አያመጣም።" የሚል ወሸመጥ ቆራጭ መልስ ነበር የሰጡት፡፡ ሆኖም የችግሩን ስፋትና ጥልቀት በማስረዳት መጨረሻ ላይ የመነሻ ሀሳቡን(ፕሮፖዛሉ)ን ለማየት እንዲልክላቸው ከአንገት በላይ ይስማሙና በቴሌግራም ይልክላቸዋል። መጀመሪያም ፍላጎት ስላልነበራቸው መልስ ሳይሰጡት ይቀራል።

ከሰባት ወር በኋላ ግን ሰሞኑን በብዙኀን መገናኛዎች እንደተከታተላችሁት ባለፈው ሐሙስ አሳሳቢው የኑሮ ውድነት የ"አዲስ ወግ" የመወያያ አጀንዳ ሆኗል። ምንም እንኳ ችግሩ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ስለሆነ መፍትሔውም በሁሉም ኢትዮጵያዊ ዙሪያ መለስ ርብርብ መፈታት ያለበት ሆኖ ሳለ የመወያያ ሀሳቡን ያቀረቡትና ያብራሩት ሁሉም የመንግስት አካላት መሆናቸውና ተወያዮችም በቂ ጊዜ ተሰጥቷቸው ሀሳቦች በነጻነት እንዳይንሸራሸሩ መደረጉ በመድረኩ ላይ ጥላ ቢያጠላበትም እንዲሁም አጀንዳነቱም የዘገዬ ቢሆንም ከእነአካቴው ከሚቀር ችግሩ መነሳቱ ይበል የሚያሰኝ ነው። ሆኖም የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፍተኛ የኢኮኖሚ አማካሪ ከሰባት ወር በፊት የኑሮ ውድነቱ አንገብጋቢ አገራዊ ጉዳይ መሆኑን አምነው ተቀብለው የተባለው አገራዊ መድረክ በወቅቱ ተዘጋጅቶ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ግልጽና ጥልቅ ምክክር ተካሂዶ የመፍትሔ ሀሳብ ቀርቦ ሁሉም የቤት ስራውን ወስዶ ቢሰራ፤ መንግስትም ቢያንስ ከዚያን ጊዜ አንስቶ ትኩረት ሰጥቶ ቢተጋ ኑሮ አሁን የገጠመንን ቀውስ ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ባንችል እንኳ ጉዳቱን መቀነስ ይቻል ነበር። ይህ ባለመሆኑ ግን እዚህ ላይ ደርሰናል።

ከፍ ብሎ ለማሳየት እንደተሞከረው ችግሮች ከመከሰታቸውና ከመባባሳቸው በፊት አነፍንፎ አበክሮ የመከላከል እና የችግር አረንቋ ውስጥ ተዘፍቀን አንገታችን ላይ እስኪደርስ የማነናቅና የማቅለል አባዜ እንደ አገር፣ ዜጋና መሪ የሚስተዋልብን ችግር ቢሆንም፤ እንደ የኢኮኖሚ ከፍተኛ አማካሪው ያሉ ትልቅ ኃላፊነት ያለባቸው ባለሙያዎች ግን እንደኔ ካለ የኢኮኖሚክስ ጨዋ ይልቅ የኑሮ ውድነት በአገር ላይ የደቀነውን አደጋ ቀድመው መረዳትና ደውሉን በመንካት መንግስትን የማንቃትና የማስረዳት ኃላፊነት ነበረባቸው። ይሄን ገጠመኝ ያነሳሁት ለክስ ወይም እንዲህ ብዬ ነበር ብሎ ለመታበይ ሳይሆን፣ መሰል የመሪዎቻችን ከፍተኛ አማካሪዎችና ባለሙያዎች ወደ ራሳቸው ወስደው ውስጣቸውን ሊፈትሹበት ይገባል፤ በሚል ቅን ሀሳብ በመነሳት መሆኑን ያጤኑአል።

በዚህ የአዲስ ወግ ወይይት ላይ የታዘብሁት ሌላው ጉዳይ የመንግስት አካላት የኑሮ ውድነቱን ለማቃለል የነበረባቸውን ድክመት አፍረጥርጠውና ዘክዝከው ተቀብለው ከስህተታቸው ተምረው አዲስ የመፍትሔ ሀሳብ ይዘው ከመምጣት ይልቅ፤ ችግሩን ውጫዊ ለማድረግ የሄዱበት ርቀት፣ ያሳዩት መፈራገጥና መጋጋጥ አስገርሞኛል። ከብሔራዊ ባንክ የመጡት ባለሙያ የዋጋ ግሽበቱና የኑሮ ውድነቱ የተባባሰው ከ1997 ዓ.ም ወዲህ መንግስት የገንዘብ ፖሊሲውን በማላላት ከፍተኛ የመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንት ውስጥ በመግባቱ ነው በማለት ችግሩን ውጫዊ ያደርጋሉ። ለውጡ ከባተ ወዲህም ተባብሶ ስለቀጠለው አሳሳቢ የኑሮ ውድነት የብሔራዊ ባንኩ ድክመት ምን እንደነበረ አምኖ ተቀብሎ በቀጣይ የነበረበትን ድክመት አርሞ ምን ለመስራት እንዳቀደና ምን እየሰራ እንደሆነ ግን በበቂ ሁኔታ አላብራሩም።

ከሕብረት ስራ ኮሚሽን የመጡት የስራ ኃላፊም ኮሚሽናቸው የኑሮ ውድነቱን ለመከላከል በነበረው ሒደት የነበረበትን ድክመት አፍረጥርጠው ከማቅረብና ከዚህ ተምሮ ምን ለመስራት እንዳሰበና ምን እየሰራ እንደሆነ በተጨባጭ ከማስረዳት ይልቅ፤ የኑሮ ውድነቱን እያባባሰው ያለው እሴት የማይጨምረው የንግዱ ተዋናይ ነው በማለት ችግሩን ውጫዊ አድርገውታል። ከፕላንና ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር የመጡ የስራ ኃላፊዎችም ያለባቸውን ድክመት ያለምንም ማቅማማት ከመቀበል ይልቅ ኮቪድ 19ኝንና የራሽያን ጦርነት የሀጢያታቸው ተሸካሚ ማድረግን መርጠዋል ። እዚህ ላይ ለኑሮ ውድነቱ መባባስ ኮቪዱም ሆነ ጦርነቱ አሉታዊ ተጽዕኖ የለውም እያልሁ ሳይሆን ችግርን ውጫዊ ከማድረግ ይልቅ የራስን ችግር ቆጥሮ ወስዶ ማረም ይቅደም ለማለት ነው።

ባለፉት ሰባት አመታት በተለይ ለውጡ ከመጣ ወዲህ የተከሰቱ ግጭቶች፣ ጦርነቶች፣ ቀውሶችና ኢኮኖሚያዊ አሻጥሮች ለኑሮ ውድነቱ መባባስ ከፍተኛ አሉታዊ አስተዋጽኦ እንዳላቸው የሚያጠያይቅ አይደለም። ሸማቹም ሆነ ሕዝብ ግን መንግስት ላይ ቅሬታ እያቀረበ ያለው በአቅሙ ልክ መስራት የሚገባውን አልሰራም በሚል እንጂ ከአቅሙ በላይና ያልተጠበቁ ውጫዊ ችግሮች የሉም አላለም ።

ሕዝብ ያለው፣ የሚችለውን ማለትም፡- በግብይት ሰንሰለቱ ከጉልት ወይም ከማሳ እስከ ጅምላ አከፋፋይ የተሰገሰገውን ደላላ ከግብይት ስርዓቱ ቆርጦ ያውጣልን፤ መሠረታዊ ሸቀጦችን በሚደብቁ አልጠግብ ባይ ስግብግብ ነጋዴዎች ላይ አስተማሪ ሕጋዊ እርምጃ ይውሰድልን፤ ዋጋን በአድማና በመነጋገር የሚውስኑ የቀን ጅቦችን ይያዝልን፤ ሙስናንና ብልሹ አሰራሮችን ከመዋቅሩ ያጽዳልን፤ በድጎማ የሚገባው መሠረታዊ ሸቀጥ ለሸማቹ በቀጥታ መድረሱን የሚያረጋግጥ አሰራርና ስርዓት ያበጅልን፤ በነጻ ገበያ ስም ስድ የተለቀቀው የግብይት ስርዓት ላይ ልጓም ያብጅልን፤ መሠረታዊ ሸቀጦች ላይ የዋጋ ተመንና የትርፍ ህዳግ ይቀመጥልን፤ የንግድና የመኖሪያ ቤት ኪራይ ተመን ይውጣልን፤ ገበያውን እንደ ወልመርት፣ አሊባባና አማዞን ላሉ የውጭ ኩባንያዎች ክፍት ያድርግልን ፤ ብልጽግናም ሆነ ተፎካካሪዎች ቄሮም ሆነ ፋኖ ከባለሀብቱ ጋር ያላቸውን መርህ አልባ ግንኙነቶች ያቋርጥልን፤ የኑሮ ውድነቱንና ግሽበቱን ታሳቢ ያደረገ የደመወዝ ጭማሪ ያድርግልን፤ ለመንግስት ሰራተኛው የታክስ ወይም የግብር ቅነሳ ያድርግልን፤ የታጠፈውና ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር የተዳበለው የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ስልጣኑና ተግባሩ ተሻሽሎለት ራሱን ችሎ ይደራጅ፤ ከሚኒስቴሩ ጋር መዋሀዱም የጥቅም ግጭት ስላለው ይታረም፤ የሸማቾችን መብት ለማስከበር ከሚንቀሳቀሱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር እጅና ጓንት ሆኖ ይስራልን ፤ ወዘተረፈ አለ እንጂ፣ ሕዝብ ከመንግስት አቅም በላይ የሆነ ነገር አልጠየቀም። ይህ ሕዝብ ምን ያህል አስተዋይና አርቆ አሳቢ እንደሆነ መቼም ቢሆን አጠያይቆ አያውቅምና።

ዛሬ እያስተዋልን ያለነው ታፍኖ ሲብላላና ሲባባስ የኖረው ቀውስ ጡዘት(climax) ላይ መድረሱን ነው። ይህ ትውልድና መንግስት በታሪክ አጋጣሚ የዚህ ጡዘት ባለዕዳ ሆኗል። የዕዳው መጠን ቢለያይም፤ በደርግ በሶሻሊዝም ስም ሕዝቡ ማህበራዊ ወረቶቹን እንዲጥል ተገደደ። ፈጣሪውን ባህሉንና ወጉ ለማስጣል ብዙ ግፊት ተደረገበት። አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ ተባብሎ ተሳስቦና ተዛዝኖ እንዳል ኖረ በዕዝ ኢኮኖሚ በአምራቾችና በኮታ ተተበተበ። ሕወሓት/ኢህአዴግ ወደ አገዛዝ ሲመጣ ደግሞ አንድን ቡድንና ጭፍራውን ተጠቃሚ ለማድረግ መዋቅራዊና ተቋማዊ ሆኖ ተሰራ። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ሌብነት እስካልተያዙ ድረስ ሙያ ነው እስከመባል ተደረሰ። ሌብነት ጀግንነት ሆነ። በአንድ ጀምበር በአቋራጭ መክበር እና ጥሎ ማለፍ እንደ ስኬት ተወደሰ። የሃይማኖት ተቋማት ሳይቀሩ በዚህ ተቃኙ።

በደርግ ጊዜ መዛበት የጀመሩ ሕዝቡን አጋምደው የኖሩ የውሃ ልኮች መናድ ጀመሩ። የሃይማኖት ወይም የትምህርት ተቋማት የዚህ መዛነፍ አካል ሆኑ። ፈሪሃ ፈጣሪም ሆነ መልካም ስነ ምግባር ከሕዝቡ የልቦና ውቅር ተደለዙ። ባለስልጣኑ፣ ተቃዋሚውና ሲቪል ሰረቨንቱም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከዚህ ቡድን እንደ አስተዋጾው ፍርፋሪ ደርሶታል። ምንም እንኳ እንደተሳትፎው መጠን የደረሰው ፍርፋሪ የተለያየ ቢሆንም። የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ሌላው ለዛሬው አጣብቂኝ የዳረገን ችግር ነው። የደርግ የዕዝ ኢኮኖሚ ፈጠራንና ሀብትን የማያበረታታ ሲሆን፤ ሕወሓት/ኢህአዴግ ደግሞ አንዴ ልማታዊ ሌላ ጊዜ ነጭ ካፒታሊስት ነኝ ቢልም ኢፍትሐዊና አንድን ቡድን ልዩ ተጠቃሚ ለማድረግ ያለመ ስለነበር ኢኮኖሚውን ለመዋቅራዊና ተቋማዊ ችግር ዳርጎታል። በሕወሓት/ኢህአዴግ የተንሰራፋው የገነገነ ሙስና አገሪቷን በቁሟ ግጦ ግጦ መለመሏን አስቀርቷታል። ከአገር ውስጥ ጥቅል ምርት እስከ 30 በመቶ የሚሆነውን ዘርፏል። ወደ 30 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋን ሀብት ከዚች ድሀ እናት መቀነት ቆረጦ አሸሽቷል። የሚያሳዝነው የዘረፍኸውን አርፈህ ብላ ቢባልም በጄ አለማለቱ ነው። ላለፉት ሃያ ሰባት አመታት በዘረፈው ሀብት አገራችንን ለማፍረስ ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም። ያልወጣው አቀበት ፤ ያልወረደው ቁልቁለት የለም።

አገዛዝ ላይ ለመቆየት ያነበረው የማንነት ፖለቲካ በዜጎች ዘንድ እንዲሰርጽ ለ30 አመታት በጀት መድቦ ተቋማዊና መዋቅራዊ አድርጎ ሌት ተቀን በመስራቱ ጥላቻ፣ አለመተማመንና መጠራጠር በመላ አገሪቷ እንደ ሰደድ እሳት ተዛመተ። በአናቱ የዘረፈውን ሀብት በመጠቀም በመላ አገሪቱ ግጭትና ብጥብጥን በመጥመቅ ለፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ዳረጋት። ይህ አልበቃ ብሎት ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በሰሜን ዕዝ ላይ ትውልድም ሆነ ታሪክም ይቅር የማይለውን ክህደት እና ለማየት የሚዘገንን ለመስማት የሚሰቀጥጥ ጭፍጨፋ ፈጽሞ አገሪቱን አስገድዶ ጦርነት ላይ ዘፈቃት። ሶስት ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አከርካሪው ቢሰበርም ግልጽ ድህረ መቐሌ ስትራቴጂ ባለመኖሩ ወታደራዊ ድሉን ማጽናትና ማዝለቅ ባለመቻሉ ሕወሓት አፈር ልሶ ከመነሳት አልፍ የአማራና የአፋር ክልሎችን በመውረር ህልቆ መሳፍርት የሌለው ሰብዓዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ ፈጥሯል።

በሁለቱ ክልሎችና በአገሪቱ ያደረሰው አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት በብዙ መቶ ቢሊየኖች የሚገመት ሲሆን ሰብዓዊና የስነ ልቦና ጉዳቱ ደግሞ እጅግ የከፋና በምንም ሊተመን የማይችል ሆኖ ሰንበሩ ለአመታት አብሮን ይኖራል። ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዳፋውም ለአመታት ማንገዳገዱ አይቀርም። ይህ አላንስ ብሎ መጀመሪያ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ እሱ ትንሽ ጋብ ሲል ደግሞ የዩክሬንና የራሽያ ጦርነት ተጨምሮ ኢኮኖሚውን እንደ ሀይለኛ የጎን ውጋት ቀስፎ ይዞታል። በአገሪቱ ከተንሰራፋው ሙስና፣ ብልሹ አሰራር፣ አልጠግብ ባይነትና ስግብግብነት ጋር ተጀምሎ የዋጋ ግሽበቱና የኑሮ ውድነቱ ዜጋውን ለረሀብና ለእርዛትና ለበሽታ ዳርጎታል። ተስፋ እንዲቆርጥ፣ መፈጠሩን እንዲጠላና እንዲያማርር አድርጓታል። በድህረ የብልጽግና 1ኛ ጉባኤ በመላ አገሪቱ በተዘጋጁ ሕዝባዊ መድረኮች ጮህ ብለው የተሰሙ ድምጾች ይሄን ሀቅ አረጋግጠዋል።

ከማህበራዊና ከፖለቲካዊ ችግርነት አልፎ የህልውና፣ የሰላም፣ የጸጥታና የደህንነት ችግር ሆኖ ከእጃችን እንዳይወጣ የቀውሱን አንገብጋቢነት በልኩ መረዳት፤ ገዥው ፓርቲም ወጥና ሀቀኛ በሆነ ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ቀውሱ የደቀነውን አደጋ ተገንዝቦ ለዙሪያ መለስ መፍትሔው ግንባር ቀደም ተሳታፊ መሆን ይጠበቅበታል። በየደረጃው ያለ ስግብግብና አልጠግብ ባይ ነጋዴም ዛሬ መሠረታዊ ሸቀጥ እየደበቀና እጥረት እየፈጠረ የሚያጋብሰውን ሀብት ነገ ሊበላው፤ ልጆቹን አስተምሮ ለወግ ለማዕረግ ማብቃት የሚችለው አገር ሰላም ሲሆን ነውና ቆም ብሎ ሊያስብ ይገባል። በሰሞነኛው አንድ መድረክ እንደተገለጸው እሱ እየበላ ጎረቤቱ እየተራበ ሊቀጥል አይችልም። ሲብስበት በሩን ሰብሮ ይገባለታል። በሕዝብ ረሀብና ችግር እያተረፈ ያለው ደላላም ቆም ብሎ ሊያስብና ወደ ህሊናው ሊመለስ ይገባል። በእርግጥ ህሊና ካለው። ቸር እንሰንብት ! አሜን።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## ቤተሰብ የመሰረተውና መልካም ሥነ ምግባር ያጎለበተው ሰብዕና

### ‹‹ሦስት ሺህ ዓመት ከኖርን ሁላችንም ድብልቅ እንጂ ከአንዱ ብሔር አልተፈጠርንም››

- ዶክተር አብርሃም አስናቀ

ጽጌረዳ ጫንያለው

**ዓለም መሪዋን ትመስላለች የሚባለው ያለ ምክንያት አይደለም። ሰርቶ ለለወጥ ያለ ሁሉ ይጠቀምባታል። አለሰራም ያለውም እንዲሁ ይሆንባታል። ግን መርምሮ የተረዳት ብቻ የሚኖርባት እንደሆነች በሕይወታቸው የተጠቀሙባት ምስክሮች ናቸው። ፈተናዋ ቢያታክትም ተስፈኛና ትግዕስተኛ የሆነ አይወድቅባትም። እንደውም እየተማረባት ዘመናትን ያልፍባታል።**

**በዚህች ምድር ለመኖር ዘመኑን መዋጀትና ራስን መሆን እንዲሁም በራስ መኩራት ብቻ አስፈላጊ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። ከእነዚህ መካከል ደግሞ ለዛሬ «የሕይወት ገጽታ» አምድ እንግዳችን ያደረግናቸው ዶክተር አብርሃም አስናቀ አንዱ ናቸው። እርሳቸው ሕይወታቸውን ደስተኛ ያደረጉት ፈተና ስለሌለ ሳይሆን ከፈተናው ተምረው፣ አውቀውና ተጠቅመው፤ ሌሎችን ጭምር ጠቅመው ነው። ሌሎችም ይህንን ማድረግ እንደሚችሉ ከሕይወት ተሞክሯቸው በመነሳት ያብራራሉ። ስለዚህም ልምዳቸውን ተጋሩ ስንል ጋበዝናችሁ።**

### ልጅነት

ተወልደው ያደጉት በአማራ ክልል ደብረማርቆስ ከተማ በ1939 ዓ.ም ነው። አባታቸው ነጋዴ ሲሆኑ፤ ዘመናዊ አስተዳደግ እንዲኖራቸው በብዙ መልኩ አግዘዋቸዋል። በዚያውም ልክ ባህላቸውን እንዳይረሱ አድርገዋቸዋል። ለዚህም ማሳያው ማንኛውም ልጅ እንደ ሕግ አታድርግ የተባለውን እንዳይፈጽሙ ማድረጋቸው ነው። ለአብነትም ሻይ ቤት መግባት፤ ቡና መጠጣት፤ ጥሬ ሥጋ መብላት አይፈቀድም። ሁሉም ልጆቻቸው ይህንን ተቀብለው ይተገብራሉ።

በእነ ዶ/ር አብርሃም ቤት ቤተሰብን በቻሉት ሁሉ ማገዝ ውዴታ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ነው። በዚህም ዘወትር ቤተሰባቸውን በተለያየ ነገር ያግዛሉ። ውሃ በመቅዳት፣ እንጨት በመፍለጥ እንዲሁም መብራት ስላልነበረ እንግዳንም ሆነ ታላላቆችን እንዲሁም እናትና አባትን ቆሞ በማብላትና እግር በማጠብ ያገለግላሉ። ከዚያ የተረፈ ጊዜ ደግሞ በጨዋታ የሚያልፍ ሲሆን፤ ማንበብና ስፖርት መስራት ፈልገው ከሚዝናኑባቸው መካከል ይጠቀሳሉ። በትምህርት ቤት ደግሞ ክርክርና እጅ ስራ፤ እንዲሁም እርሻ ትምህርት የሚመርጧቸውና የሚሳተፉባቸው ናቸው።

በባህሪያቸው ዝምተኛ ሲሆኑ፤ መዋሸትና መስረቅ በፍጹም አይወዱም። ለዚህ ደግሞ መሰረቱ አስተዳደጋቸው እንደሆነ ያስረዳሉ። የአካባቢው ልጆች በቤተሰብ ሳይሆን በአካባቢው ነዋሪ ሁሉ የሚያድግ በመሆኑ የመመሳሰል ጠባይም አላቸው። ማህበረሰቡ ልጄ ብሎ ስለሚያሳድጋቸው የሁሉም ልጅ በመሆናቸውም እነርሱም በዚህ ልክ ለሁሉም ያገለግላሉ። የሚገስጻቸው ብዙ በመሆኑም ከስህተታቸው ይመለሳሉ።

በዚህ አስተዳደግ ውስጥ ማለፋቸው ደግሞ ለዛሬው ማንነታቸው ብዙ ነገር አበርክቶ አለው። አንዱና ዋነኛው ሰውን መውደድ ሲሆን፤ መታዘዝና ለሌላም ማሰብ ስንቃቸው እንዲሆን አስችሏቸዋል። ተካፍሎ መብላትና አቋም ያለው ሰው መሆንም ልጅነታቸው የሰጣቸው ትልቁ በረከት ነው። ሌላው መምህራንን ከምንም በላይ ማክበርና የሚሉትን መስማት ሲሆን፤ የልጅነት ፍላጎታቸውን ሳይቀር እነርሱ የሚወስኑላቸው እንደነበሩና በዚያም ስኬታማ እንደሆኑበት ያስረዳሉ።

### ትምህርት

ዶክተር አብርሃም በአባታቸው ጥረት ትምህርት ወዳድ ሆነዋል። የትምህርትን ዋጋ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ሁሉም ልጆቻቸው እንዲማሩ ይፈልጋሉ። በዚህም ትምህርታቸውን አሀዱ እንዲሉ በዚያው በተወለዱበት አካባቢ ንጉስ ተክለሃይማኖት ትምህርት ቤት እንዲገቡ አድርገዋቸዋል። እስከ አስረኛ ክፍልም የተማሩት በዚሁ ትምህርት ቤት ነው። ጥሩ የሚባሉ ተማሪም ነበሩ። ከዚያ የተሻለ ትምህርት ፍለጋ ወደ አዲስ አበባ የላኳቸው ሲሆን፤ ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ገብተውም እስከ 12ኛ ክፍል ተምረዋል።

የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ውጤት ሳይመጣ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች አገር ለመጎብኘት ገንዘብ አዋጥተው ጉዞ በጀመሩበት ወቅት ጎንደር መማርን የተመኙት ባለታሪካችን፤ ውጤት ለማምጣት ከባድ ቢሆንም እርሳቸው ለዚህ አልተበገሩምና የአሰቡት ቦታ ለመሄድ ችለዋል። በጊዜው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጎንደር ጤና ጥበቃ ኮሌጅ ይባል ነበርና በዚያ ገብተው የጤና መኮንንነት ትምህርት መማር ችለዋል። ስልጠናው ለአራት ዓመት ያህል የቆየ እንደነበርም አጫውተውናል።

ትምህርት ለእርሳቸው ልዩ ዋጋ እንዳለው የሚያነሱት ዶክተር አብርሃም፤ እየሠሩ መማር ይፈልጉ ነበር። ሆኖም ግን የድህረ ምረቃ ትምህርት በጊዜው በአገር ደረጃ አይሰጥም። የውጭውም ቢሆን በቀላሉ አይገኝም። ስለሆነም ጊዜ ቢወስድም እየፈለጉ መቆየታቸውን መረጡ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያሉም አዲስ አጋጣሚ ተፈጠረ። ይህም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሕክምና ፋካሊቲ ጤና መኮንኖችን ተቀብሎ በሀኪምነት የሚያሰለጥን መሆኑ ነው። በብዙ ፈተና ውስጥ ቢያልፉም ነገሮች ተስተካክለው ተፈላጊውን መስፈርት በማሟላት ትምህርት እንዲጀምሩ ሆኑ።

እንግዳችን የሕክምና ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ያልሞከሩት የተግባራዊ ልምምድ አልነበረም። በዚህም ሙሉ ኃላፊነት ጭምር ተሰጥቷቸው ቀዶ ሕክምና አድርገዋል። ጎንደር ጤና ኮሌጅንም ሲቀላቀሉ ይህንኑ ተግባር በስፋት አከናውነዋል። ይህ ደግሞ ሌላኛውን የትምህርት ምዕራፍ እንዲያዩ አስችሏቸዋል። ትምህርቱ የቀዶ ህክምና ሲሆን፤ በኢትዮጵያ የድህረ ምረቃ ትምህርት ሲጀመር በአገራቸው ለመማር ያመለከቱበት ነው። ሆኖም ጊዜው እንዳለፈ ተነገራቸውና ሳይሳካ ቀረ። ነገር ግን ተስፋ መቁረጥን ስለማያውቁ በእንግሊዝ አገር ለመማር አመልክተው መጠበቅ ጀመሩ።

ፍላጎት ያለው ሰው በማንኛውም መልኩ ሳይታክት ከሞከረ አጋጣሚዎች ሰፊ እድል ይሰጣሉ የሚሉት ባለታሪካችን፤ የእንግሊዙ ምላሽ ሳይመጣ እጃቸው ላይ ሌላ እድል ከተፍ አለ። ይህም ከምስራቅ ጀርመን ጋር በቅርበት ይሰሩ ነበርና እኛ ጋር ሄደህ ለምን አትማርም የሚል ነው። እድሉን ምንም ሳያቅማሙ ነበር የተቀበሉት። ነገር ግን የሚሰሩበት ኮሌጅ ሊለቃቸው አልፈለገም። ‹‹አንተን የሚተካ ሌላ ሰው ሳይመጣ አትሄድም›› ብሏቸዋል። በብዙ ትግል ግን ሁኔታዎች ተስተካከሉላቸው። ወደ ጀርመን ሄደውም በዚያ ለመማር ቋንቋ ግድ ነውና ተማሩ። ከዚያ የቀዶ ሕክምና ትምህርቱን ገቡበት። በጣም ከባድና ፈታኝ ቢሆንም እርሳቸው ቀደም ሲል ልምዱ ነበራቸውና በቀላሉ ሊወጡት ቻሉ።

ቀጣዩ የትምህርት ምዕራፍ የሚወስደን ወደ ካናዳው ማጊል ዩኒቨርሲቲ (McGill University) ሲሆን፤ ከፍተኛ የቀዶ ሕክምና ትምህርትን የተከታተሉበት ተቋም ነው። ጥሩ ልምድ የቀሰሙበት፤ ለአገራቸውም የተረፉበት እንደነበርም ያስታውሳሉ።

### ተዘዋዋሪው ሥራ

የመጀመሪያ ሥራቸውን አሀዱ ያሉት በጎጃም ጠቅላይ ግዛት መተከል ጤና ጣቢያ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በር በአሁኑ አጠራር ቻግኒ ላይ ነው። በጤና መኮንንነት ተመድበውም ነው ያገለገሉት። ሥራው በአስተዳደሩ ላይ ብቻ ሳይሆን ክፍተት ባለበት ሁሉ ነው። ምንም እንኳን አዳዲስ ነገሮች ቢገጥሟቸውም ይህንን በትጋትና በንቃት ተወጥተውታል። የመንደር ጤና አገልግሎት ጭምር በመሥጠት ያገለገሉም ናቸው። ሱዳን ጫፍ ድረስ እየተጓዙም ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል።

ከአንድ ዓመት አገልግሎት በኋላ ደግሞ ወደ ተማሩበት ኮሌጅ ተመልሰው በመምህርነት አገልግለዋል። በኮሌጁ ውስጥ ጤና መኮንኖችን፣ የማህበረሰብ ነርሶችንና የጤና ተቆጣጣሪዎችን አሰልጥነዋልም። በተጨማሪም በማሰልጠኛ ጤና ጣቢያዎች ጭምር እየሄዱ የተመደቡትን ተማሪዎች በሳምንት አንድ ቀን ይቆጣጠራሉ፤ ያሰለጥናሉ፤ ችግራቸውንም ይፈታሉ። የማሰልጠኛ ጤና ጣቢያዎቹ ተቆጣጣሪ ቦርድ ሊቀመንበር ሆነውም አገልግለዋል።

ከሕክምና ትምህርት በኋላ የገቡትም እዚያው ጎንደር ጤና ጥበቃ ኮሌጅ ውስጥ ሲሆን፤ መኖሪያ ቤት ሳይኖራቸው ሆቴል ተከራይተው ጭምር የቀዶ ሕክምናውን ተግባር ሲያከናውኑ ነበር። ይህ የሆነበት ምክንያት ከእርሳቸው በፊት የነበረው ሕንዳዊ ቀዶ ሀኪም ስለሄደ ነው። ስለዚህም የአገራቸውን ክፍተት ደፍነው ቀን ብቻ ሳይሆን ሌሊቱን ጭምር ማገልገል ችለዋል። የክፍለ አገሩ ቀዶ ህክምና ባለሙያ በመሆናቸው ያለ እረፍት ቢሰሩም አንዳንድ ቢሮክራሲዎች በእጅጉ ያማርሯቸው ነበር። ሥራ እስከማቆም የደረሱባቸውን ጊዜያትም ነበሩ። በተለይም የቤት ጉዳይ፤ የኃላፊዎች ጣልቃ ገብነት በጣም ፈተና ሆኖባቸው እንደቆየ ያስታውሳሉ።

ጤና ጥበቃና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሐኪሞችን ሳያነጋግሩ እንዲሁ በየራሳቸው በሐኪሞቹ እንቅስቃሴና ክፍያ ላይ የሚወስኑት ነገርም እርሳቸውን ዋጋ ካስከፈሏቸው መካከል ይጠቀሳሉ። ሁመራ የሄዱበት አጋጣሚ ደግሞ ለዚህ ጥሩ ማሳያ እንደነበርም ያነሳሉ። ማንም ምንም ሳይነገራቸው ሄደው ልብሳቸው ሳይቀር እላያቸው ላይ እስኪበሰብስ ሠርተዋል። በእርግጥ በሰሯቸው ተግባራት ደስተኛ ናቸው።

ሁመራ ላይ ጦሩ በቂ የሕክምና ማዕከል ስለሌለው ወደ ኤርትራ ከመግባቱ በፊት አንድ የቀዶ ህክምና ሆስፒታል ያስፈልገዋልና እርሳቸው ይህንን በማቋቋሙ በኩል ብዙ ለፍተዋል። ከዘመቻ በላይ ዘመቻ በማድረግም ነው ተግባሩን የፈጸሙት። እንደውም የውሃ ጉዳይ ፈተና ሆኖባቸው ነበር፤ ውሃ ለማስገባት ጠዋትና ማታ እየቆፈሩ ጭምር ሆስፒታሉን እውን አድርገዋል።

እንግዳችን ከሁመራ በኋላም ቢሆን ወደነበሩበት ሥራ አልተመለሱም፤ እንደ ዘማች ወደ ተሰነይ ጉዞ ጀመሩ እንጂ። ተሰነይ ያለው ጦር በተላላፊ በሽታ ተይዟል በመባሉ እርሳቸው እንዳይመለሱ አድርጓቸዋል። በዚህም ወደ ቦታው በማቅናት የበሽታውን መንስኤ ፈትሸው ሕክምና ከመስጠት ጎን ለጎን የከተማው ውሃ መሳቢያ ተነቅሎ ተወስዶ ስለነበር እንዲተካ አደረጉ። ጦሩም ሆነ ሌላ የህብረተሰብ ክፍል ውሃውን ከተጠቀመ ደግሞ አፍልቶ መሆን እንዳለበት አስጠነቀቁ። በዚህም በአጭር ጊዜ መፍትሄ መጣ። ይህ ሲጠናቀቅ ደግሞ አሁንም ወደ አቆርዳት እንዲሄዱ ታዘዙ።

ሆስፒታሉ ሁሉም የሕክምና ቁሳቁስ የተወሰደበት በመሆኑ ያንን ሙሉ እንዲያደርጉ ግዴታ ተጣለባቸው። ነገር ግን የጦር ክፍሉ ኃላፊዎች በብዙ መንገድ ፈቃደኛ ሊሆኑላቸው አልቻሉም። ሆስፒታሉ በቁስለኛ እስኪሞላ ድረስም ነገሮች አልተስተካከሉላቸውም። "ከዚህ በኋላ አልጠየቅም፤ ወደ አስመራ ወስዳችሁ ማሳከም ትችላላችሁ" የሚል ውሳኔ ሲያሳልፉ ነገሮች ተቀየሩ። የተባሉት ነገሮችም በቅጽበት ውስጥ ተሟሉ። እርሳቸውም ሥራቸውን በአግባቡ ፈጸሙ። ከቤት በድንገት ከወጡ ደግሞ ስምንት ወር ተቆጥሯል። ነገር ግን አሁንም አትሄድም ተባሉ። ይህንን ግን መታገስ አልቻሉም ነበር። አስመራ የሚሄዱበትን መንገድ ያመቻቹትና ጤና ጥበቃ ሚኒስትሩን ያነጋገሩበት ምስጢርም ይኸው ነው።

ሚኒስትሩን በደብዳቤ የጠየቁ ሲሆን፤ መልሱም ‹‹አስመራ መካነ ሕይወት ሆስፒታል የሚሰሩ የወዳጅ ሀገር የቀዶ ህክምና ቡድን በቅርቡ ስለሚመጡ እነርሱን አስተምረህ ትመለሳለህ›› የሚል ነበር። በዚህም ተስፋ ሳይቆርጡ ጠበቁ። የተባሉትን አድርገው ሲጨርሱ ግን ሌላ ቅራኔ ገጠማቸው። ከኤርትራ ጤና ጽህፈት ቤት ኃላፊ የይለፍ ደብዳቤ ሲጠይቁ እንቢ ተባሉ። እርሳቸውም አልሰራም ብለው አመጹ። ከወራት በኋላም ሙያቸው የግድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በልመና ገብተው እንዲሠሩ ተደረገ። በመጨረሻም የፈቃድ ደብዳቤ ቤታቸው ድረስ መጣላቸው። ወደ ጎንደርም ተመለሱ።

ከዘመቻ መልስ ከመደበኛ ሥራቸው በተጨማሪ ሐኪሞችን የማሰልጠን ሥራ ለመሥራት ዝግጅት የጀመሩት እንግዳችን፤ ስሙ ተቀይሮ ጎንደር ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በተባለው ውስጥ መሥራታቸውን ቀጠሉ። ይሁንና ብዙም ሳይቆዩ ለትምህርት ወደ ጀርመን አቀኑ። ከዚያ መልስ ጎንደር ሳይመለሱ አዲስ አበባና መሰል ከተሞች ላይ እንዲሠሩ ሆኑ። ለዚህ ምክንያቱ ሁለት ነበር። የመጀመሪያው ቤተሰባቸው ላይ በደል መድረሱ



ፎቶ ፦ ገባው ገብሬ

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ



ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ያለ ምንም መረጃ አገሩን ጥሎ ጠፋ መባላቸው ነው።

አገር ያስተማረችው ልጅ አገሩን እንጂ ሌሎችን ማገልገል የለበትም ብለው የሚያምኑት ዶክተር አብርሃም፤ ጎንደር መሥራት አለበት ቢባልም ባለመቀበላቸው ለአምስት ወር ያህል ያለ ሥራ ተቀምጠዋል። በመጨረሻ ለማዕከላዊ ፕላን ቢሮ የሰው ኃይል ክፍል «አገሪቱ ለቀዳጅ ሀኪም ከጎንደር ውጭ ቦታ ስለሌላት ቪዛ ተሰጥቶኝ ሌላ አገር ሄጄ እንድሰራ ይፈቀድልኝ» የሚል ደብዳቤ አስገብተው ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የካቲት 12 ሆስፒታል እንዲመድባቸው ሆነዋል።

ከአራት ወር የሥራ ላይ ቆይታ በኋላም አዲስ አበባ ሊመደብ አይገባውም የሚለው ጭቅጭቁ ዳግመኛ በመነሳቱ ወደ ጅማ የተላኩት እንግዳችን፤ ብዙም ሳይቆዩ ለእረፍት አዲስ አበባ በመጡበት ወቅት ለአስቸኳይ ሥራ አሰላ ሄደው እንዲያገለግሉም ሆነዋል። ቀጣዩ የሥራ ቦታቸው ጦር ኃይሎች ሆስፒታል ውስጥ ሲሆን፤ የቀዳጅ ሀኪም እጥረት ስላጋጠመ የተመደቡበት ነው። አምስት ወር ያህልም በቦታው ላይ ሠርተዋል። ይህ ሁኔታ ደግሞ በአዲስ አበባ የመሥራታቸውን ነገር አረጋግጦላቸዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትሩን ሹፌር የማከም እድል ገጥሟቸው ነበርና የሆስፒታሉ ዳይሬክተር ጸሐፊና ሹፌሩ ስለሚግባቡ በእርሷ አማካኝነት ጫናና እንግልታቸው እንዲታይላቸው ሆኗል። በዚህም በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ተመደቡ። የህክምና ዳይሬክተር ሆነውም ያገለግሉ ጀመር። ከካናዳ መልስም እንዲሁ ከዚሁ ሳይወጡ ሠርተዋል። በወቅቱ የህክምና ዳይሬክተሩ ሥራውን ለቆ ነበርና ከዋና ሥራቸው ጋር ደርበው እንዲሰሩ ተደርገዋል። ከዚያ በተጨማሪ የድህረ ምረቃ ትምህርት በመጀመሩ ምክንያት የቀዶ ህክምና ሀኪሞች ይፈለጉ ነበርና እርሳቸውም በድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት እንዲሰሩ ሆኑ። በእርግጥ ፈልገው አልገቡበትም። በፕሮፌሰር አስራት ጉትጎታና ትግል ነው ተግባሩን የፈጸሙት።

እርሳቸው ዳይሬክተር በነበሩበት ወቅት የፓርቲ አባል መሆን ያሾማል፤ ያሽራልም። ስለዚህም እርሳቸውም በዚያ ውስጥ እንዲካተቱ ይፈልጋሉና ኃላፊ አደረጓቸው። ነገር ግን አልተቀበሉትም ነበር። ማንኛውም ሙያ መመራት ያለበት በውድድር በመጣ ሰው ነው ብለው ያምናሉና አሻፈረኝ አሉ። ተግባራቸው ያልጣማቸው የበላይ ኃላፊዎችም በተለያየ መልኩ መከራን ያበዙባቸው ጀመር። በገዛ ፈቃዳቸው የመልቀቃቸውም ምስጢር ይህ እንደነበር ያስታውሳሉ።

እንግዳችን ጳውሎስ ሆስፒታልም በኃላፊነት አገልግለዋል። ሆስፒታሉ የማስተማሪያ ሆስፒታል በመሆኑ በዩኒቨርሲቲው ቀዶ ህክምና ኃላፊ ትዕዛዝ የቀዶ ሕክምና ክፍልንና ትምህርቱን በኃላፊነት መርተዋል። በተመሳሳይ በጳውሎስ ያሉ መምህራን ዘውዲቱ ያሉትንም ሰልጣኞች ይደግፉ ነበርና ያንንም አድርገዋል። አሰራሮች አልመችህ ሲላቸው ደግሞ ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርገው በመተው ፊታቸውን ወደ ግል ሆስፒታሎች አዙረዋል። ለረጅም ጊዜም በግል ሆስፒታሎች ላይም አገልግለዋል፤ እያገለገሉም ነው። በትርፍ ሰዓታቸው ደግሞ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ በቦርድ ሊቀመንበርነት፣ በአባልነትና በበጎ አድራጎት ድርጅቶች ውስጥ ሠርተዋል።

ሥራ ወዳድነታቸው ብዙ አጋጣሚዎችን የሚፈጥርላቸው እንግዳችን፤ ሱዳን ዳርፉር በመሄድ የሠሩበት አጋጣሚ ለዚህ አንዱ ማሳያ ነው። ወዳጃቸው የሆነ አንድ የአፍሪካ ሕብረት ሕክምና ኃላፊ ለደረጃ አንድና ሁለት የህክምና ተቋማት የሚያስፈልጉ ቁሳቁስ ዝግጅት ላይ እንዲሳተፉ አደረጋቸው። ፕሮጀክቱ በዋናነት አፍሪካውያንን ብቻ የሚይዝ ስለነበር በአራት ቀን መዘጋጀት አለበት ተብለው የገቡበትም ነው። የህክምና ቡድን አደራጅተውም ተግባሩን እውን አድርገውታል። ይሁን እንጂ በቀላሉ የለቀቃቸው አልነበረም። መሬት ወርዶ ይሰራበት ሲባልም ከአንተ ውጭ አይሆንም ተባሉ። በብዙ ትግልም ስምምነት ላይ ደረሱ። ለአፍሪካዊያን የሚጠቅመውን ይህንን ፕሮጀክት ከቡድኑና ከጓደኞቻቸው ጋር ሆነውም ተፈጻሚ አደረጉት።

## ኃላፊነትና እይታቸው

ሙያ በአካዳሚክ ውጤት አይለካም። ጥሩ ውጤት ያመጣ ሁሉ በተሰማራበት ልክ ውጤታማ ሊሆን አይችልም። የሰዎች የማገናዘብና መፍትሄዎችን ቀድሞ የመመልከት ልክ ነው ለስኬት የሚያበቃው። አንድ ሰው ያለ ፍላጎት እዚህ ሙያ ላይ ይግባ መባሉም ትክክል አይደለም። ሰዎች ለዚያ ሙያ ዝንባሌ ከሌላቸው ኃላፊነታቸውን ሊወጡ አይችሉምና። ያልወደዱትን ሙያ ተገደው ስለሚሰሩ ውጤታማም አይሆኑም። ከሁሉም በላይ ደግሞ ሙያውን ከገንዘብ ጋር እንዲያይዙት ይሆናሉ። ስለዚህም የሙያው ፍቅርን እንዲያስቀድሙና በኃላፊነት እንዲሰሩ ፍላጎት የመጀመሪያ መስፈርት መሆን እንዳለበት ያስገነዝባሉ።

ሰራተኞች የሙያ ስነ ምግባራቸውን እንዲያከብሩ ለማድረግ ሁለት መሰረታዊ ነገሮች ያስፈልጋሉ። አንደኛው ልጆች ከልጅነታቸው ጀምረው በስነ ምግባር የታነጹ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። ከልጅነት ጀምሮ የተሰራ ሰው ሰው እንጂ ሌላ አይሆንም። ለዚህ ደግሞ ወላጅ፣ ትምህርት ቤት እና የሃይማኖት ተቋማት ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። በማህበረሰቡ እሴትና ባህል ተኮትኩቶ እንዲያድግ የተቻላቸውን ሁሉ ማድረግ አለባቸው። ይህ ካልሆነ ግን የገቡበትን ሙያ ስነ ምግባር ሊያከብሩ አይችሉም።

ሌላው በሁሉም ሙያ ውስጥ ያሉ የበላይ ሃላፊዎች ምሳሌ መሆን ይኖርባቸዋል። ያለዚያ ግን ታችኛውን ሰራተኛ በስነምግባር ማነጽም ሆነ ኃላፊነቱን እንዲወጣ ማድረግ አዳጋች ነው። በተመሳሳይ ሰራተኞችም ቢሆኑ ማህበረሰቡን ፊደል ያልቆጠረ በመሆኑ እንደ እውቀት ምንጭ አለመቁጠራቸው ትክክል አይደለም። የተማረ ሊቅ እንጂ አዋቂ አይባልም። አዋቂ ማለት ለገንዘብ ሳይሆን ለማህበረሰብ ደስታ የሠራ ነው። ለእድገት፣ ለሰላም፣ ለተቸግሩ የሚደርስ ሰው ነው። ማህበረሰቡን አንድ ላይ እንዲቆይ የሚያደርግም ነው። በተለይም ስነ ምግባርን ከባህል፣ ከእምነት እና መሰል አካባቢዊ ነገሮች ጋር አዋህዶ የሚጓዝ ከሆነ እርሱ በሥነ ምግባር ያደገ ነው።

የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታውም እንዲሁ አንዱ ኃላፊነታችንን በአግባቡ እንዳንወጣ የሚያደርገን እንደሆነ የሚጠቁሙት ዶክተር አብርሃም፤ የምዕራባዊያን የትምህርት ስርዓት እኛን የሚያውቅ አይደለም። ይሁን እንጂ ትክክል ነው በማለት በቀጥታ እንጠቀምበታለን። ይህ ደግሞ ሳናውቀው እንድንሰራበት ያስገድደናል። እናም ከዚህ ለመውጣት የእኛን ታሪክ፤ ባህልና አሰራር አጎልብተን የሚያስፈልገንን በመጨመር መጓዝ አለብን። ይህ ካልሆነ ግን በአለው የትምህርት አሰጣጥ የግለሰብ እንጂ የቤተሰብ አለያም የአገርን ችግር ልንፈታ አንችልም። ለምሳሌ በግብርና የተመረቁ ልጆች ማህበረሰቡን ለማገዝ ወደ ገጠር በሄዱ ጊዜ የእርሻ መሳሪያዎችን እንኳን አያውቁም። በሌሎች ሙያዎችም ተመሳሳይነት ያለው ተግባር እናያለን። ስለሆነም ይህ ከምን መጣ የሚለውን መመርመር እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ።

አሁን ላይ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ሙያውን አክብሮ የመስራት ወይስ ጥቅማጥቅምን አስቦ መንቀሳቀስ ስንል ሰፊውን ቦታ የሚይዘው በተለይም ከኃላፊነት ጋር ተያይዞ ጥቅማጥቅም ነው። ለዚህ መነሻው ደግሞ ድህነት እንደሆነ ይታመናል። ለቁሳቁስ ያለን ፍላጎት ያየለ ነው። እናም ሙያችን ከገንዘብ እኩል ሊስተካከል አልቻለም። ፍቅሩ በልጦ ቢሆን ግን በገንዘብም አንደለልም። እናም ይህ የሚሆንበትን መሰረት ከልጅነት ጀምሮ ማቆም አስፈላጊ መሆኑን ይናገራሉ።

ኃላፊነት ከአለቃ፣ ከሥራ ዝርዝርና መሰል ነገሮች በላይ ነው፤ እስከቻልንና ማንንም እስካልጎዳ ድረስ የምንከውነው ሊሆን ይገባል። ያልተገለጹ ኃላፊነቶችን ጭምር ለሙያችን ክብር ስንል መሥራት አለብን። ይህ ሲሆንም ነው ማህበረሰብንና አገርን መጥቀም የምንችለው። የሌሎችን ኃላፊነት በተሸከምን ቁጥር የእኛንም የሚያግዝ ይፈጠራልና ቀና ሆኖ ማገልገል ልምዳችን ይሁን። ሰው መጠንቀቅ ያለበት ፉክክር ውስጥ መግባትን ነው። ያን ጊዜ ሥራውም ሆነ ኃላፊነቱ ስኬታማ ይሆናል ይላሉም።

ኃላፊነት ከወንበርና ጠረጴዛ ይልቅ ሥራን ማስረከብም መረከብም ልምድ ማድረግ ነው። ከዚያ በህሊናችን ልክ ማሰራት ይሆናል። ይህንን ጊዜ ውስጣዊ እርካታ፣ ጤና፣ ሰላምና ሌሎች እድሎች ይመጣሉና እንጠቀምባቸውም ምክራቸው ነው።

## መልእክት

አገር የሚኖረው የማህበረሰቡ አካል መሆናችንን ስናስብ፣ ባህሉ ሲገዛንና በዚያ ቦታ መፈጠራችንን ማመንና ላሉ ችግሮች መፍትሄ ማበጀት ስንጀምር ነው። ራሳችንን ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ኢንተርናሽናል (አለማቀፋዊ) እያደረግን የምናጠፋው ጊዜ መኖር የለበትም። ለአብነት እንደ አገር 80 በመቶ የሚሆነው ጊዜ የሚጠፋው እኛን በማይመለከተን ጉዳይ ነው። የሌሎችን እያዩ መጎምዠት መቼም አይለውጠንም። እኔ የምቆፍረው ወይም የማለማው መሬት ከሌለኝ አገሬ ምን ትሰራልኛለች፤ ቤት የምሰራበት ቦታ ከሌለኝ አገሬ ምን ጠቀመችኝ የሚለው አስተሳሰብም የመነጨው ከዚህ አንጻር ነውና ብዙ መሥራት ያለብንን ጊዜ በዚህና መሰል ጉዳዮች አናባክነው መልእክታቸው ነው።

ሌላው ያነሱት ሀሳብ በብሔር መከፋፈላችንን እናቁም የሚለው ነው። ሦስት ሺህ ዓመት ከኖርን ሁላችንም ድብልቅ እንጂ ከአንዱ ብሔር አልተፈጠርንም። ስለሆነም የዘር ግንዳችን ኢትዮጵያ ብቻ ነው። እንደውም እንደ አገር ብቻ ሳይሆን እንደ ሰው ልጅ መፈጠርም መሰረት እኛ ብቻ ነን። ስለዚህም የእንትና ብሔር ብሎ ማነስ እኛን አይመጥነንምና አናድርገው። ዛሬ የተከፋፈልነው በብሔር ሳይሆን በቋንቋ መሆኑን ማመን ይገባናል። ይህ ደግሞ አስተዳደግ እንጂ ተፈጥሮ አላመጣውምና በተፈጥሮ እንግባባ። በህክምና በቤተሰብ እየጠበብን ስንመጣ ለበሽታ እንጋለጣለን። ስንራራቅ ደግሞ በሽታው ሊጠፋ ይችላል። ስለሆነም መስፋታችን ጤናችን እንደሆነ አምነን ውበታችንን እናጉላው ሲሉ መልእክታቸውን ያስተላልፋሉ።

እንደ አገር ችግሩ የሕዝብ ሳይሆን የፖለቲካ ልሂቃን እንደሆነ የሚያነሱት ዶክተር አብርሃም፤ የእነዚህ ፖለቲከኞች ሥራ ራሳቸውን ማቆየት እንጂ ሕዝብን ከችግር ማውጣት አይደለም። ለሕዝብ ነው የሚሉ ከሆነ ታች ወርዶ መስማትንና መሥራትን ልምዳቸው ማድረግ አለባቸው። ሕዝብ ሲሰቃይ ሳይሆን ሲለወጥም መሰረት መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባቸዋል። ነገር ግን ዛሬ ላይ እየሆነ ያለው ከዚህ በተቃራኒ ነው። በማይገባ ንግግራቸው ሕዝብን ያደማሉ፤ ያሳምጻሉም ያጥላላሉም። ይህ ደግሞ ፖለቲካው ለሕዝብ እንባ አባሽ እንዳይሆን ያደርገዋል። ስለሆነም ቆም ብለው ያስቡ በማለትም ይመክራሉ።

የሙብት መከበር ከራስ ይጀምራል። ለማንም የሚሰጥ አይደለም። እናስከብርልህ የሚሉም አጭበርባሪዎች እንጂ አዳኞች አይደሉም። አንተ የት ሄደህ እነርሱ ያስከብሩልሃል? እነርሱ መጀመሪያ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ይወጡ። ያልሆነውን ሆነህል ከማለትም ይቆጠቡ። መኪናና ብሩ ብቻ ሳይሆን ከዚያ በላይ ያለውን ኃላፊነት ተረድተው ለሕዝብ ይስሩ። ያን ጊዜ ለራሳቸውም፣ ለሕዝባቸው እድል ይሰጣሉ። አገርንም አሸናፊ ያደርጋሉ የሚለውም ሌላው መልእክታቸው ነው።

የውጭው ዓለም ከእኛ በብዙ መልኩ ይለያል። አንዱን ብቻ ብናነሳ ተካፍሎ መብላትን አያውቅም። ለሌሎች መስጠትንም እንዲሁ። ለእናቱ ጭምር የማይራራ ነው። በምሳ ሰዓት ምሳ እየበላ እናቱ ብትመጣ አብረን እንብላ ሳይሆን የሚለው የእኔ ብቻ ነውና ሱፐር ማርኬት ሄደሽ ገዝተሽ ብይ ነው። ይህ ደግሞ ለማንም እንደማይሆን በግልጽ ያሳየናል። በተለይም እንደ እነ አሜሪካ አይነት አገሮች በእጅ አዙር ከእኛ የሚፈልጉት ነገር ከሌላቸው ሊያስፈራሩንም ሆነ ሊደግፉን አይችሉም። እናም አሁን ቆም ብለን የምናስተውልበት ጊዜ ነውና የምናሸንፍበትን መንገድ እንቀይስ። አንድነትና ባህላችንን ተጠቅመው ይህንን ፈታኝ ጊዜ ማለፍ ይኖርብናል። እኛ ተቸግረን ለልጆቻችን አዲሷን ኢትዮጵያን ማስረከብም የውዴታ ግዴታችን ነውና እናድርገው ምክራቸው ነው።

አውሮፓውያን ከግል ፍላጎታቸው በስተቀር በምንም አይደራደሩም። አንድ አገር ጥሬ እቃ አቅራቢ ከሆነ ዘላለም ያንን ብቻ ያድርግ ባይ ናቸው። አድጎ ሥራቸውንና ጥቅማቸውን እንዲነጥቃቸው አይፈልጉም። በሌላ መልኩ የእነርሱ ገንዘብ በሁሉም ሁኔታ ዋጋ እንዲያገኝ ይሠራሉ። ስለዚህም አሁን በጫና ውስጥ እንድንሆን በተለያየ መልኩ የሚሠሩት እያደግን እንደመጣን ስለተመለከቱ ነው። እናም ነቅተንና ታጥቀን ይህንን ትግላችንን ማስቀጠል ይገባናልም ሌላው መልእክታቸው ነው።

እኛ መሆን ያለብን በታሪክ ተማሪና ታሪክን አስቀጣይ እንጂ አምላኪ አይደለም። አምላኪነት በበፊቱ ታሪክ አሁንን መኖር ነው። ያ ደግሞ ምን ያህል ዋጋ እያስከፈለን እንደሆነ በሚገባ አይተነዋል። እናም ተማሪ ሆነን መልካሙን በመያዝ ስህተቱን ባለ መድገም ወደፊት መጓዝ ከምንም በላይ ያስፈልገናል። ለእኔም ሆነ ተበደልኩ ለሚለው አካል በታሪክ መከሰሳችን መፍትሄ ሳይሆን ለሌሎች ቀዳዳ መክፈትና የእለት ሆዳችንን አለመሙላት ነውና ልብ እንበለው ሲሉ ይመክራሉ።

በመጨረሻ ያነሱት የራሳችንን ወዳዶች መሆን እንዳለብን ነው። በተውሶ የሰለጠነ አንድም አገር የለምና ያንን እናድርገው። እኛ አገር እየተመረተ በእነርሱ ቋንቋና ፊደል እየሸጥንላቸው ማንነታችንን አንቅበረው። የስልጣኔ ምንጭ ጀማሪ መሆናችንን እናስፋበት እንጂ አናቅለውም ሲሉ መልእክታቸውን ያስተላልፋሉ። እኛም መልእክታቸው ይፈጸም በማለት ለዛሬ አበቃን። ሰላም!

# «ገበታ ለአገር» - ወንጪ ደንዲ ኢኮ ሎጅ

**ዳግም ከበደ**

በኢትዮጵያ ለቱሪስት መስህብነት የሚሆኑ ታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊ ስፍራዎች በእጅጉ በርካታ ናቸው። የሰው ዘር መገኛ ምድር ከመሆኗ አንፃር በእጅጉ ሲበዛ አስደናቂ ሃብቶች ባለቤት መሆኗ ያን ያህል አስገራሚ አይሆንም። ይሁን እንጂ ዓለማችን ላይ በጎብኚዎች መዳረሻነት ከሚታወቁት አገራት ተርታ ግን ለመሰለፍ አልቻለችም። በባህላዊ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊ እሴቶቿ በብዙ እጥፍ የምታስከነዳቸው አገራት ሃብቶቻቸውን የመጠበቅ፣ የማስተዋወቅና ምቹ መሰረተ ልማት በመገንባት የመንከባከብ ተግባር በመስራታቸው ብቻ ቱሪዝም የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽና የጀርባ አጥንት እንዲሆን አስችለውታል።

"በእጅ የያዙት ወርቅ እንደ መዳብ ይቆጠራል" ይሉት አባባል ለዘመናት ሰቅዞ የያዛት አገር የቱሪዝም ዘርፉን እሴቶች ከመረዳትና ከዚያም ተጠቃሚ ከመሆን ይልቅ ማንቀላፋትና ዳዴ ማለትን ምርጫዋ አድርጋ ቆይታለች። ጥረት ተደርጎ ይቅርና እንዲያው በደብዛዛውም ቢሆን ከተለያዩ ዓለም ክፍል በአገሪቱ የሚገኙ ድንቅ ድንቅ የቱሪዝም ሃብቶችን ከመጎብኘትና ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በመደነቅ ምስክርነታቸውን ከመስጠት አልቦዘኑም። ይህ ነው የሚባል የአገር ውስጥ ጎብኚ ባይኖርም ቅሉ በአገራቸው ሃብት ኮርተው ዙሪያ ገባውን በመቃኘት ዓለም ትኩረት እንዲሰጠው የሚሞግቱም አልጠፉም።

ዛሬስ? በዚህ ወቅት ቱሪዝምና መዳረሻ ስፍራዎች በማልማት፣ በማስተዋወቅ ጎብኚዎችን በመሳብ እንዲሁም አዳዲስ መዳረሻዎችን በመፍጠር ከሃያላኑ ተርታ የሚያሰልፍ ጠንካራ ኢኮኖሚና እጅግ ተወዳጅ አገርን መፍጠር እንደሚቻል ሁሉም ያምናል። ለዚህም ነው ከከፍታው ማማ ላይ በክብር ለመቀመጥ የቱሪዝም ዘርፉን ከዋና ዋና ምሰሶዎች ዘርፍ የሚያስቀምጡት።

የኢትዮጵያ መንግሥት በቅርቡ ቱሪዝም ከአምስቱ ዋና ዋና ዘርፎች መካከል ቀዳሚው መሆኑን በመግለፅ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ እንደሆነ ይፋ አድርጓል። በተለይ የመስህብ ስፍራ የሆኑት መዳረሻዎችን በማልማት፣ አዳዲስ ስፍራዎችን በመፍጠር፣ ታሪካዊ ቅርሶችን፣ ተፈጥሯዊ ሃብቶችን በመጠበቅና ለጎብኚዎች ክፍት የማድረግ ስራዎች መከናወናቸውን አሳውቋል። በተለይ "ገበታ ለአገር" በሚል ሃሳብ የአዲስ አበባ ተፈጥሯዊ ቦታዎችን በማልማት፣ በተወዳጅ መልከአ ምድር ባላቸው "የኮይሻ፣ ጎርጎራና ወንጪ" አካባቢዎች ላይ ታላላቅ ግንባታዎችን ለማድረግ እቅድ ነድፎ ወደ ትግበራ መግባቱን መረጃዎች ያሳያሉ። ይህ ጥረት ለዘርፉ መነቃቃትን የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ ኢትዮጵያን በተጨማሪ ሌላ ገፅታ ለማስተዋወቅ እንደሚረዳ በዘርፉ ላይ ልዩ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

የዝግጅት ክፍላችን በዛሬው የባህልና ቱሪዝም አምድ ላይ የኢትዮጵያ መንግስት "በገበታ ለአገር" ፕሮጀክት ስር ከያዛቸው ሜጋ የቱሪዝም መዳረሻ ስፍራዎች ውስጥ አንዱ የሆነውን "የወንጪ ደንዲ ሃይቅ" የመዳረሻ ልማት ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ ይመለከታል። የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅም ከሳምንት በፊት በስፍራው ተገኝቶ የተመለከተውንና ፕሮጀክቱን የሚመሩትን አካላትና አመራሮች አነጋግሮ ያገኘውን ምላሽ እንደሚከተለው ያቀርበዋል።


### ገበታ ለአገር «ወንጪ ደንዲ»

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በገበታ ለአገር በመጀመሪያው ዙር ካስቀመጧቸው ፕሮጀክቶች ወንጪ ሐይቅ አንዱ ነው፡፡ ጎብኚዎች ወደ ሥፍራው ቢያቀኑም፣ ያለውን የተፈጥሮ መስህብ ያህል ጥቅም ያልሰጠው ወንጪ ሐይቅ በተፈጥሯዊ መስህብ ተወዳጅ ከሆኑት ስፍራዎች መካከል ነው፡፡

በኦሮሚያ ክልል ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን በወንጪ ወረዳ የሚገኘው ወንጪ ሐይቅ፣ ከአዲስ አበባ በምዕራብ 150 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በወሊሶና አምቦ መሀል ይገኛል። የዝግጅት ክፍላችን ዘጋቢ በስፍራው ተገኝቶ እንደተመለከተው በመጀመሪያው ምእራፍ የወንጪ ደንዲ ሃይቅ መዳረሻን የማልማት ሥራ የመንገድ ጠረጋ፣ የሎጅ ግንባታና የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታዎች እየተከናወኑ መሆኑን ተመልክቷል።

ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው "በገበታ ለአገር" የቱሪዝም መስህብ ስፍራዎች ዙሪያ በሰጡት ማብራሪያ ወቅት ስለ ወንጪ ደንዲ ኢኮ ሎጅ በተናገሩበት ወቅት





ፎቶ-ዳግም ከበደ

**በግንባታ ላይ የሚገኘው የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም ከትልልቅ መዳረሻዎች መካከል አንዱ ነው፤**

እንደሌሎቹ ፕሮጀክቶች በታቀደለት ጊዜ ለማከናወን በስፍራው የሚንቀሳቀሱት የሸኔ የሽብር ቡድን አባላት እንቅፋት መሆናቸውን ገልጸዋል። ይህን እንቅፋት ለመፍታትና አካባቢውን ለማልማት ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ እንደነበር አሳውቀው ነበር። ይህን ማብራሪያ ከሰጡ በኋላም በየደረጃው ያሉ የፀጥታ አካላት፣ አመራሮችና የፕሮጀክቱ አስፈፃሚዎች "የተቀናጀ ሥራ በመሥራት የመዳረሻ ስፍራውን የማልማት እንቅስቃሴ ቀጥሏል" በማለት በስፍራው ተገኝቶ ሁኔታውን ለቃኘው የዝግጅት ክፍሉ ዘጋቢ አስረድተዋል። ለመሆኑ ይህ እስኪጠናቀቅ በጉጉት የሚጠበቀው ሜጋ የቱሪዝም መዳረሻ ስፍራ ምን ደረጃ ላይ ይገኛል? ለጥያቄ የዞኑ አመራሮች፤ የፕሮጀክቱ አስፈፃሚዎችና የአካባቢው ነዋሪዎች ይህን ይላሉ።

"የወንጪ ደንዲ ኢኮ ሎጅ የመንገድ ሥራ እየተፋጠነ ነው" የሚሉት ፕሮጀክቱ የደረሰበትን ሁኔታ ለመመልከት የልኡክ ቡድናቸውን አስከትለው በስፍራው የተገኙት የጨፌ ኦሮሚያ የገጠር ልማት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ድሪሳ ዋቁማ ናቸው። እንደ እርሳቸው ገለፃ፤ የግንባታ ሂደቱ ከዚህ ቀደም በካሳ ክፍያና ከጸጥታ ችግር ጋር በተያያዘ ምክንያቶች ተጓትቶ እንደነበር ይናገራሉ። አሁን ግን ችግሮቹ ተለይተው አቅጣጫ ከተሰጠ ወዲህ በታቀደለት መሰረት በአፋጣኝ ሁኔታ ግንባታዎቹ እየተከናወኑ መሆኑን መመልከታቸውን አስረድተውናል። በተለይ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶቹን በርካታ ማሽነሪዎችን በማሰማራትና ማሻሻያ በማድረግ የክረምት ወቅት ከመግባቱ በፊት አብዛኛውን ክፍል እንዲጠናቀቅ ቋሚ ኮሚቴው አቅጣጫ መስጠቱን ገልጸዋል።

"ከአሁን ወዲህ የካሳ ክፍያና የፀጥታ ችግር ምክንያት ሊሆን አይችሉም" የሚሉት የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ተጠናቆ አካባቢው የቱሪስት መዳረሻ የማይሆን ከሆነ የኮንትራክተሮቹ ችግርና ፕሮጀክቱን የሚያስፈፅሙት አካላት የክትትል ችግር እንደሚሆን ይናገራሉ።

### የፕሮጀክቱ ምንነን ያካትታል

የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም ፕሮጀክት የመሰረተ ልማት ፕሮጀክት ማናጀር አቶ ብርሃኑ ተስፋዬ እንደሚገልፁት፤ የወንጪ ደንዲ ኢኮ ሎጅ ሶስት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት። አንደኛው በወንጪ ሃይቁ አካባቢ የሚሰራ፣ ሁለተኛው በደንዲ ሃይቅ አካባቢ እንዲሁም በወንጪና ደንዲ መካከል የሚሰራ ሁሉን አቀፍ የቱሪዝም መዳረሻ ስፍራ ነው ።

"ከአንድ አመት በፊት ዲዛይን ቀረፃ ላይ ትኩረት አድርገን ስንሰራ ቆይተናል" የሚሉት የፕሮጀክት ማናጀሩ፤ ኤም ኤች ኢንጂነሪንግ ሃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር እንደሰራው ይገልፃሉ። አሁን ላይ በወንጪ አካባቢ የሚሰሩ ሎጆች፣ የመንገድ ዲዛይንና የተራራ መውጫ ስፍራዎች ዲዛይኖች መጠናቀቁን ይገልፃሉ። በደንዲና በሁለቱ ሃይቆች መካከል በሚገኘው ስፍራ የሚሰራው የቱሪዝም መዳረሻ የሆቴል፣ ሎጅ እንዲሁም መሰል የመስህብ ስፍራ ዲዛይኖችም በዚሁ ካምፓኒ አማካኝነት መጠናቀቁን ይገልፃሉ። ከእነዚህ ውስጥ በረጅም ጊዜ የሚለሙ ፕሮጀክቶች መኖራቸውን በማንሳትም አሁን ላይ በቅርብ ጊዜ ተሰርተው እንዲጠናቀቁ እቅድ የተያዘላቸውን ክፍሎች እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

"ከወንጪ ሃይቅ ጋር በተገናኘ መንገዶችና በአካባቢው 18 ሎጆች ለመስራት ታስቦ በሂደት ላይ ነው" የሚሉት የፕሮጀክቱ ማናጀር፤ የሃይኪንግ (ተራራ መውጣት)፣ ፍልውሃ፣ የሚኒራል ውሃ እንዲሁም ፏፏቴን የሚያለሙ ክፍሎችን መያዙን ይናገራሉ። በወንጪ ሃይቅ ላይ በአሁኑ ሰዓት የመንገድ፣ የሎጅ እንዲሁም የመብራት ሥራ ግንባታዎች መጀመራቸውን በመግለፅ፤ የመንገድ ግንባታውን በሁለት ተቋራጭ እየተሰራ ሲሆን የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝና የቻይና ኮንስትራክሽን ኮምኒኬሽን ካምፓኒ መሆናቸውን ይናገራሉ። የግንባታ ሂደቱ ከካሳ ክፍያና ከጸጥታ ችግር ጋር የተወሰነ መጓተት ቢታይበትም አሁን በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ ግንባታውን በማፋጠን እስከሚቀጥለው ክረምት ዋና ዋና ሥራውን ለማጠናቀቅ ታቅዶ እየተሰራ መሆኑንም ያነሳሉ።

"የመንገድ ሥራው የቱሪስት መዳረሻ ልማት አካል ከመሆኑ አንጻር የአካባቢውን ተፈጥሮ በተስማማ መንገድ በጥንቃቄ እየተከናወነ ነው" የሚሉት አቶ ብርሃኑ የአስፋልት፡ የፓርኪንግና የመሮጫ ትራክን ጭምር አካትቶ ግንባታው እየተፋጠነ መሆኑን ያነሳሉ። በአንዳንዱ አካባቢ ከ18 በመቶ እስከ 42 በመቶ የመንገድ ግንባታ ሂደት ላይ መሆኑን አንስተው ከሃሮ ከተማ እስከ ወንጪ ሃይቅ ያለውን ክፍል በአገር በቀሉ የመከላከያ ኢንጅነሪንግ ኢንተርፕራይዝ እየተከናወነ መሆኑን ያነሳሉ። በዚህም የቆረጣና አፈር ሙሊት ሥራው እስከ 70 በመቶ ድረስ እንደተጠናቀቀ ገልፀው ዋናውን የሚይዘው የማጠቃለያ ስራው በመሆኑ በጥቅሉ 18 በመቶ እንደያዘ ይናገራሉ። እስከ መጪው ክረምትም መንገዱን ክፍት ለማድረግ እየተሰራ ነው። ሁለተኛውን የመንገድ ሥራ የያዘው የቻይና ኮንስትራክሽንም ከሃሮ ወንጪ ተራራውን ዞሮ ፤ ከወንጪ ወደ ደንዲ እንዲሁም የማራቶን ትራክን ጨምሮ ሶስት መንገዶችን የሚሰራ ሲሆን ሂደቱም 42 በመቶ መድረሱን ይናገራሉ።

የወንጪ ደንዲ ኢኮ ሎጅ በስፔን ማድሪድ ተካሂዶ በነበረው በ24ኛው የዓለም የቱሪዝም ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የ2021 ምርጥ የቱሪዝም መንደር ሆኖ መመረጡ ይታወሳል። በሶስት ምዕራፎች ተከፍሎ እንደሚሰራ የተነገረው ፕሮጀክቱ የመጀመሪያው ምዕራፍ በአንድ ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ የነበረ ሲሆን ግንባታው ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶ ተጓትቶ ነበር።

### የማህበረሰቡ ተሳትፎ ለምን ያስፈልጋል?

አቶ ታዬ ጉዲሳ የደቡብ ምእራብ ሸዋ ዞን አስተዳዳሪ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም እንደ አገር እየተሰሩ ካሉ ትልልቅ የቱሪዝም መዳረሻዎች መካከል አንዱ ነው። የአካባቢው ነዋሪ የነበረው ጥያቄ የተመለሰው በዚህ ፕሮጀክት መሆኑን በማንሳትም በዚህ መልኩ ስራው መጀመሩ ለአካባቢው ሕዝብና ለኢትዮጵያ ሳይሆን ለዓለም የቱሪዝም መስህብ ስፍራ ተጨማሪ ሃብት እንደሆነ ይገልፃሉ።

"በአካባቢው ያለው ህብረተሰብ ከፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ነው" የሚሉት የዞኑ አስተዳደር፤ ይህንን ህብረተሰቡ ተረድቶ እንቅፋት እንዳይፈጠርና የሰላም እጦት እንዳይኖር ሌት ተቀን መጠበቅ እንዳለበት ነው የሚገልፁት። እስካሁንም አንፃራዊ ሰላም የተገኘው በመንግሥት የፀጥታ ሃይል ብቻ ሳይሆን ህብረተሰቡ እራሱ የአካባቢውን ሰላም ለማስጠበቅ እየሰራ በመሆኑ ነው። ይሄ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና ከዓለም የቱሪዝም መንደሮች መካከል ምርጡ መዳረሻ ተብሎ እውቅና ያገኘው ስፍራ አሁን ካለው በተሻለ የጎብኚዎች መዳረሻ እንዲሆን ጥሪ አቅርበዋል። የፌደራል መንግስትም አሁን ካለው በተሻለ መልኩ የአካባቢው ፀጥታ እንዲጠበቅ ተጨማሪ ድጋፍ ማድረግ እንዳለበት በማሳሰብ ሃሳባቸውን ይቋጫሉ።

### እንደ ትዝብት

የዝግጅት ክፍላችን ዘጋቢ በስፍራው ሲገኝ ከፍተኛ የፀጥታ ጥበቃ በክልሉ ሃይሎች ሲደረግ ተመልክቷል። ይህ ሊሆን የቻለው በስፍራው ሰርገው የሚገቡ የሸኔ ሽብር ቡድን አባላት እንዳሉና ጥቃት እንደሚፈፅሙ ስለሚታሰብ ነው። እንደሚታወቀው ቱሪዝም ምንም አይነት "ኮሽታ" የማይፈልግና ፍፁማዊ ሰላምን የ ሚፈልግ ነው። በመሆኑም የቱሪዝም መዳረሻ ልማቱን በውቡ መስህብ ወንጪ ላይ መስራትና መመረቅ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ዘላቂ ሰላምን ማስፈን ያስፈልጋል። ይህ ካልሆነ ግን ከፍተኛ የአገር ሃብት ወጥቶበት አልቆ በሰላም እጦት ምክንያት ጎብኚዎች እንዳሻቸው ገብተው የማይወጡ ከሆነ ከንቱ ልፋት ይሆናል። በመሆኑም ማህበረሰቡን በማወያየት፣ ከፍተኛ የፀጥታ ሥራ በመስራትና ጎብኚዎች ስጋት እንደማይገባቸው ማረጋገጫ በመስጠት የታሰበውን ታላቅ አገራዊ አላማ ማሳካት ይገባል እንላለን።

# ሳምንቱን በታሪክ

## የበጋው መብረቅ

**ዋለልኝ አየለ**

ይህ ሳምንት አንድ ታላቅ ጀግና ያስታውሰናል። በፋሽስት ጣሊያን ወረራ ጊዜ የአገራቸውን ነፃነት ለማስጠበቅ የተዋጉና በኢትዮጵያ የአርበኝነት ታሪክ ውስጥ ደማቅ ስም ያላቸው ጀግና ናቸው ።በተለይም አገራዊ አንድነት በማጠናከር የነበራቸው ሚና ከፍተኛ ነበር። ኢትዮጵያን ከፍ በማድረግም ይታወቃሉ ። ለዚህም ጀግንነታቸው «የበጋው መብረቅ» የሚል ቅጽል ስም ተሰጥቷቸዋል ።

እኚህ ጀግና ሌተናል ጀኔራል ጃገማ ኬሎ ናቸው። ያረፉት ከአምስት ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት የካቲት 29 ቀን 2009 ዓ.ም ነው ።

የተወለዱት ጥር 21 ቀን 1913 ዓ.ም በቀድሞው አጠራር በጅባትና ሜጫ አውራጃ፣ በደንዲ ወረዳ ዮብዶ በተባለ ስፍራ ነው። አባታቸው ኬሎ ገሮ (አባ ጃገማ) የሕፃኑ ጃጋማ መወለድ እጅግ ከፍ ያለ ደስታ አሳደረባቸው ።« ... ለሰባ ዓመታት ሙሉ የጠበቅሁት አንበሳ ይህ ነው ... የፈረሴን ስም ሰጥቼዋለሁ» ብለው «ጃገማ» ብለው ስም እንዳወጡለት ይነገራል ።

ሕጻኑ ጃጋማ በተወለደ በዓመቱ እናቱ ወይዘሮ ደላንዱ በአካባቢው ተከስቶ በነበረ በሽታ ምክንያት በመሞታቸው በአክስቱና በሞግዚት እንዲያድግ አባቱ ወሰኑ ።አክስቱም ጃገማን ከወንድሙ ጋር ፀበል አስጠምቀው፤ ቄስ ቀጥረው ዳዊት እንዲማር አደረጉ። በ1923 ዓ.ም ደግሞ አባቱ ኬሎ ገሮ (አባ ጃገማ) አረፉ።

ጃገማ ገና በለጋ እድሜው «አባቱ የመረጠው» እየተባለ ለዳኝነት መቀመጥን፣ ፈረስ ግልቢያን፣ ጦር ውርወራን፣ ምክክቶሽን፣ ጋሻ አነጋገብን፣ ረሀብንና ውሃ ጥምን መቋቋምን፣ ውሃ ዋናን ... እየተማረ በጥሩ ስነ ምግባር አደገ ።በልጅነት ዘመኑ ስለቅድመ አያቱ ጎዳና ነሞ የጀግንነት ታሪክ በተደጋጋሚ ስለሰማ እርሱም እንደቅድመ አያቱ ጀግና መሆንን ያልም ነበር፡፡

ፋሺስት ኢጣሊያ በ1928 ዓ.ም ኢትዮጵያን ስትወር ጃገማ ገና በ15 ዓመቱ አርበኛ ሆኖ የፋሺስትን ጦር ለመፋለም ወሰነ ።ከአጎቱ ልጅ አሰፋ አባ ዶዮ ጋር ወደ ጫካ ገቡ ። እህቱና ወንድሞቹም ተከተሉት። ገበሬዎች፣ ወታደሮች፣ ሾፌሮች ... ከጃገማ ጋር ተቀላቀሉ። አሰፋ አባ ዶዮን ጨምሮ መጀመሪያ ከጃገማ ጋር ለአርበኝነት የወጡ ብዙ ወጣቶች በቤተሰቦቻቸው ተግሳፅ አማካኝነት ከጫካ ወጥተው ወደ መንደራቸው ቢመለሱም ጃገማ ከእርሱ



**ሌተናል ጀኔራል ጃገማ ኬሎ**

በእድሜም ሆነ በሌሎች ነገሮች የሚበልጡ በርካታ ሰዎችን በስሩ ማሰለፍ ቻለ፡፡

የጃጋማ አባት በአካባቢው ዘንድ ይወደዱና ይከበሩ ስለነበር የአካባቢው ሕዝብ በታዳጊው ጃገማ የሚመሩትን አርበኞች በልዩ ልዩ መንገዶች ያግዝ ነበር ።አርበኞቹም በፋሺስት ጦር ላይ ድንገተኛ ጥቃት በመሰንዘር ጦሩን መፈተን ጀመሩ ።ፋሺስቶች ጥይት የሚጭኑባቸውን እንስሳት በመምታት ፋሺስቶችና ባንዳዎች ሲሸሹ አርበኞቹ መሳሪያና ጥይት እየሰበሰቡ ማከማቸት ቀጠሉ ።ጣሊያኖችም ጃገማንና ተከታዮቹን ለመደምሰስ ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም ።

አርበኞቹ በጊንጪና አካባቢው በነበረው የፋሺስት ጦር ላይ ተደጋጋሚ ጥቃት በመሰንዘራቸው ጣሊያኖች በጊንጪና በአካባቢው ጠንካራ ምሽግ ሰርተውና ጦራቸውን ጠምደው ተቀመጡ ።ሐሮታና ጀልዱ የነበረው የጠላት ጦር ግንኙነት ፈጥሮ ስለነበር አርበኞቹ መተላለፊያ መስመሩን ለመቁረጥ ጥቃት ሰነዘሩ። ከጥቃቱ ባገኙት መሳሪያም ትጥቃቸውን አጠናከሩ። የጃገማ ተከታዮች ቁጥራቸው ጨመረ ። ፋሺስቶች ተጨማሪ ምሽጎችን ለመገንባት ቢያስቡም ቀድመው በገነቧቸው ምሽጎች ውስጥም እንደልባቸው መንቀሳቀስ ሳይችሉ ቀሩ ።አርበኞቹ በሚያዝያ ወር 1931 ዓ.ም ሐሮታና ጀልዱ የነበረውን የጠላት ጦር ግንኙነት ለመበጣጠስ የወሰዷቸው እርምጃዎች አዲስ አበባ ድረስ ተሰሙ፤ ብዙ የነፃነት ተዋጊዎችም እነጃገማ ያሉበት ድረስ ሄደው ተቀላቀሉ፡፡

በጃገማ የሚመራው የአርበኞች ጦር ምዕራብ ሸዋ በነበረው የኢጣሊያ ጦር ላይ ተደጋጋሚ ጥቃት በመክፈት ብዙ ጉዳቶችን አደረሰበት ።አርበኞቹ ድንገተኛ ጥቃቶችን ሰንዝሮ በፍጥነት ከአካባቢው በመሰወር የጠላት ጦር ጥይት እንዲያባክን በማድረግ፣ የአካባቢው ሰው ከፋሺስት ወታደሮችና ከባንዳዎች ላይ ጥይት እንዲገዛ በማስተባበርና ጥይት በጫኑ እንስሳት ላይ ጥቃት ፈፅሞ ጥይቱን በመውሰድ የመሳሪያ ክምችታቸውን ያጠናክሩ ነበር ።

በጥቅምት ወር 1933 ዓ.ም ጃገማን ለማጥቃት ወደ ሰንጎታ ተራራ የሄደው 350 የፋሺስት ጦር ጃገማ በሚመራቸው 17 አርበኞች ተሸነፈ። የጃገማ አርበኞች ብዙ የጠላት ወታደሮችን ገደሉ፤ ባንዳዎች የዘረፉትን ንብረት አስመለሱ፤ ወታደሮችንና መሳሪያ ማረኩ። የጃገማ ጀግንነትም እየገዘፈ ሄደ ።የአካባቢው ሕዝብም የጃገማን ጀግንነት ከቅድመ አያቱ ጀግንነት ጋር እያነፃፀረ በማውራት በጠላት ጦር ካምፕ ውስጥ ፍርሃቱ እንዲጨምር አደረገ። ወደ ወሊሶ ሄዶ በአካባቢው ከፋሺስት ጦር ጋር ሲዋጉ ወደነበሩት ወደ ደጃዝማች ገረሱ ዘንድ ሄደ። የፋሺስት ጦር በደጃዝማች ገረሱ ላይ ውጊያ ከፍቶ ስለነበር ጃገማም በውጊያው ላይ ተሳትፎ የማታ ማታ ድሉ የአርበኞቹ ሆነ። ደጃዝማች ገረሱም « ... አንተን የመሰለ ጀግና የወለደች እናት ትባረክ ...» ብለው ጃገማን አመሰገኑት።

ጃገማ በአንድ ውጊያ ላይ የማረከውን የኢጣሊያ ወታደር እንዳይገደል አድርጎ ስለአርበኞቹ ኃይል እንዲሁም ስለፋሺስቶች ፈሪነትና አረመኔነት ከነገረው በኋላ «ከምርኮኝነት ነፃ የምትወጣው ለጥይት መግዣ የሚሆነኝን 10ሺ ሊሬ ከከፈላችሁኝ ብቻ ነው» አለው። በአንድ ኢጣሊያዊ መልዕክተኛ አማካኝነት ጃገማ 10ሺ ሊሬ ተቀብሎ ምርኮኛውን ፈታው ። ምርኮኛውም ወደጦር ሰፈሩ ሄዶ ስለጃገማ ጀግንነት ለአለቆቹ ሲነግራቸው ደስ ባለመሰኘታቸው ወደ ሌላ ስፍራ አዛውረውታል ።

ጃገማ በአርበኝነት ዘመኑ ከፈጸማቸው አኩሪ ገድሎች መካከል የፋሺስት ጦር ይመካበት የነበረው የአዲስ ዓለም ምሽግ ሰበራ ፈፅሞ የሚዘነጋ አይደለም። ጃገማ ደጃዝማች ገረሱን ለመርዳት ወደ ወሊሶ ሄዶ በነበረበት ወቅት « ... ጃገማ ያን የተመካከርንበትን ጉዳይ ጨርሻለሁና ዛሬ ነገ ሳትል ሰራዊትህን ይዘህ ቶሎ ና ...» የሚል መልዕክት ከስመ ጥሯ የውስጥ አርበኛ ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ ደረሰው። ጃገማም በፍጥነት ወደ አዲስ ዓለም አቅንቶ የምሽግ ሰበራው የጦር አዝማች ሆነ ።ጥቃቱን አፈፃፀም የሚያሳይ መመሪያ ለባልደረቦቹ አስረድቶ የሥምሪት ትዕዛዞችን ሰጠ ።ራሱ ምሽጉ ውስጥ ገብቶ ቦምብና ሌሎች መሳሪያዎችን ይዘው የነበሩ የፋሺስት ጦር ባለስልጣናትን ገድሎ የመሳሪያ ዝርፊያው እንዲፈጸም አደረገ፤ እስረኞችንም አስፈታ ።በዘመቻው ላይ ከአርበኞቹ ወገን የሞቱት ሁለት ሰዎች ብቻ ነበሩ። ከጠላት ወገን ግን ከ100 በላይ ጣሊያናውያንና ጠባቂዎቻቸው ተገድለዋል ።

በመጋቢት ወር 1933 ዓ.ም ጃገማ የጭልሞን ምሽግ ከቦ በፋሺስት ጦር ላይ ተኩስ ከፈተ። «እጃችሁን ካልሰጣችሁ አንላቀቅም!» የሚል መልዕክትም አስተላለፈ። «እንደራደርና እጅ እንሰጣለን» ካሉ በኋላ አዘናግተው ሊያመልጡ ሲሉ ከአርበኞቹ ተኩስ ተከፈተባቸውና 13 የኢጣሊያ ወታደሮችና አንድ ሺ 500 ባንዳዎች ተማረኩ። ጊንጪ በጃገማ አርበኞች ቁጥጥር ስር ዋለች። ወዲያውኑም ጃገማ የኢጣሊያ ጦር የሚተማመንበት የሐሮታ ምሽግ ላይ ጥቃት እንዲከፈት አዘዘ። የጠላት ጦር አንድ ጊዜ እየሸሸ፤ ሌላ ጊዜ እያጠቃ መፋለሙን ቀጠለ ።በዚህ ጊዜ ጃገማ ብቻውን ሆኖ ቦታ እየቀያየረ መድፍ ሲተኩስ የፋሺስት ጦር ተስፋ ቆርጦ ለመጨረሻ ጊዜ ሸሸ፤ ከሞት የተረፈውም ተማረከ። የጃገማ ጦር በድል አዲስ ዓለም ገባ። ሆለታንም በቁጥጥሩ ስር አደረገ፡፡

ከግንቦት 1934 ዓ.ም ጀምሮ ሆለታ ገነት ጦር ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት በመግባት የውትድርና ስልጠና አጠናቆ የሻለቃነት ማዕረግ አገኘ ።ከዚያም ለጥቂት ጊዜያት ያህል በአምቦና በቢሾፍቱ ተመድቦ አገልግሏል ።ከዚያም በአምባላጌና በራያ አዘቦ በግዳጅ አፈፃፀም ላይ ባሳየው ብቃት በሜጀር ጀኔራል አበበ ዳምጠው ተመስክሮለት ሻለቃ ጃገማ የብርጌድ አዛዥ ሆኖ ተሾመ ።

በ1947 ዓ.ም የሌተናንት ኮሎኔልነት ማዕረግን አገኘ ። የዩጎዝላቪያ ፕሬዝደንት የነበሩት ማርሻል ቲቶ ኢትዮጵያን በጎበኙበት ወቅት የተደረገላቸውን የክብር ሰልፍ የመሩት ሌተናንት ኮሎኔል ጃገማ ነበሩ ።

በ1953 ዓ.ም የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ወቅት የመፈንቅለ መንግሥቱን ሙከራ ለማክሸፍ ለጥቃት የተንቀሳቀሰው ኃይል አዛዥ ሌተናንት ኮሎኔል ጃገማ ኬሎ ነበሩ። በ1958 ዓ.ም የሜጀር ጀኔራልነት ማዕረግን አግኝተዋል። በ1965 ዓ.ም ደግሞ የብሔራዊ ጦር አዛዥ ሆነው ተሹመዋል ።

በፈረስ ስማቸው «አባ ዳማ» የሚባሉት፣ ሌተናንት ጀኔራል ጃገማ አንድ ወንድና አምስት ሴት ልጆችን አፍርተዋል ።ጀግናው ሌተናንት ጀኔራል ጃገማ ኬሎ መጋቢት 29 ቀን 2009 ዓ.ም. አርፈው፣ ሥርዓተ ቀብራቸው እሑድ፣ ሚያዝያ 1 ቀን 2009 ዓ.ም. በአዲስ አበባ መንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል፡፡

## የደመናው ሰዓሊ

ሌላው በዚህ ሳምንት የሚታወሱት ሰው ደግሞ እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ናቸው፡፡ አርቲስቱ ያረፉት ልክ በዛሬዋ ቀን ከአሥርት ዓመታት በፊት ሚያዚያ 2 ቀን 2004 ዓ.ም ነው፡፡

እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ የተወለዱት በቀድሞው አጠራር ሸዋ ጠቅላይ ግዛት፤ በአሁኑ ሰሜን ሸዋ በምትገኘው አንኮበር ጥቅምት 13 ቀን 1925 ዓ. ም ከአባታቸው አቶ ተክሌ ማሞ እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ፈለቀች የማታወርቅ ነው፡፡

የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአዲስ አበባ፣ እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርታቸውን በእንግሊዝ አገር በሚገኘው የሥነ ጥበብ አካዳሚ በሥነ ስዕል በቅርፃ ቅርጽና በሥነ ሕንፃ ዲዛይን ተከታትለዋል፡፡

በነበራቸው የሥነ ስዕል ዝንባሌ ታላላቅ ሥራዎችን የሰሩ ሲሆን፤ ወጣትነት ዘመናቸው በ1957 ዓ.ም ከክቡር ዶክተር ከበደ ሚካኤል ጋር ከኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ እጅ የመጀመሪያውን የኢትዮጵያ የሥነ ጥበብ ተሸላሚ ለመሆን ችለዋል፡፡ ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ የአራት ዓለም አቀፍ አካዳሚዎች አባል ሲሆኑ በተሰማሩበት የሥነ ሥዕል ጥበብ በዓለም ላይ ከፍተኛ ሚና ለተጫወቱ ታላላቅ ሰዎች የሚሰጠውን «የዓለም ሎሬት» የተሰኘውን ማዕረግ አግኝተዋል፡፡ ከዘጠና ሰባት በላይ የዓለም አቀፍ ሽልማቶችን ከተለያዩ ተቋማት አግኝተዋል፡፡

በስዕሎቻቸውም፤ ሥርዓተ አምልኮን፣ ማኅበራዊ አኗኗር የማኅበረሰቡን ደስታና ሃዘንና ጀግንነቱን ሥልጣኔውንና አገር ወዳድነትን የሚያንጸባርቁ ሥራዎችን አበርክተዋል፡፡ በተለይም ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካላቸው ጥልቅ ፍቅርና እምነት በመነጨ ለተለያዩ ቤተ ክርስቲያናት እንዲሁም በስቱዲያቸውና በጸሎት ቤታቸው የሚገኙ መንፈሳዊ ስዕላትን አበርክተዋል፡፡ ከሥራቸው መካከልም በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ በግድግዳ ላይ የተሠሩ መንፈሳዊ ስዕላትን በቀለም ቅብ፣ በባለቀለም ጠጠሮች፣ በክርክም መስታወቶችና በሞዛይክ ከታወቁትና ስመ ጥር ከሆኑት ሰዓሊ ብላታ እምአዕላፍ ኅሩይ ጋር ሠርተዋል፡፡ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ሙዚየሞች ውስጥም ስዕሎቻቸው በክብር ተቀምጠውላቸው በጎብኚዎች እየታዩ ይገኛሉ፡፡ ኢትዮጵያን በማስተዋወቅ ረገድም በስዕሎታቸውና በቅርፃ ቅርጾቻቸው አማካይነት ከፍተኛ ሚና የነበራቸው ሲሆን «ቪላ አልፋ» የተሰኘው ባለ 22 ክፍሎች መኖሪያ ቤታቸውና የግል ስቱዲያቸው ውስጥ ይህንኑ ለማንጸባረቅ ጥረት አድርገዋል፡፡

በቪላ አልፋ ስቱዲዮ ውስጥ የአክሱም ሐውልት፣



**እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ**

የጎንደር ፋሲለደስ፣ የሐረር ግንብ፣ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣ ቅዱሳት ስዕላት፣ የተወለዱበት አንኮበር የሚገኘው ቤተ መንግሥት የሚያስደንቁ ባህላዊ፣ ታሪካዊ፣ ሃይማኖታዊና አገራዊ እሴቶችን አካቶ የያዘ ነው፡፡ ቪላ አልፋ ዛሬም በሥዕል ማሳያነት እያገለገለ ይገኛል፡፡

እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ በአንድ ወቅት ለኢትዮጵያ ሬዲዮ እንደተናገሩት፤ በልጅነታቸው የሰማይ ደመናን አንጋጠው በመመልከት ይመሰጡ ነበር፡፡ ደመናው የተለያየ አይነት ቅርጽ ሲሰራ በተፈጥሮ ይደመማሉ። ማነው እንዲህ በተለያየ ቅርጽ የሚሰራው እያሉ በልጅነት አዕምሯቸው ይጠይቃሉ፤ ይፈላሰፋሉ፡፡ ይህን የሰማይ ደመና መመሰጥ ወደ መሬት አውርደው እርሳቸው ደግሞ የሥዕል ሸራ ላይ መመሰጥ ጀመሩ፡፡ እነሆ የዓለም ሠዓሊም ሆኑ፡፡

እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አፈወርቅ ተክሌ እነሆ በእነዚህ ሥራዎቻቸው ይታወቃሉ፡፡

በአፍሪካ ሕብረት አዳራሽ መግቢያ የሚታየው በመቶ ሃምሳ ካሬ ሜትር ላይ የተሳለው ትልቅ የመስታወት ስዕል፣ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል የሚገኘውን የመጀመሪያውን የ«ዳግም ቀረበው» ፍርድ ስዕል፣ በሐረር የልዑል ራስ መኮንን ሐውልት፣ በአዲግራት የ«ዳግም ምጽዓት» ፍርድ ስዕል፣ በለንደን «ታወር ኦፍ ለንደን» የቅዱስ ጊዮርጊስ ጸሎት ቤት ከብር እና ከእንጨት የተሠራ የመንበር መስቀል፣ በሩሲያ፣ አሜሪካ እና በሴኔጋል ኤግዚቢሽን ላይ የቀረበው «የመስቀል አበባ» ስዕል፣ «እናት ኢትዮጵያ»፣ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ምስል እና «ደመራ» ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

# ሙሉ ባንድ የሆነው ድምጻዊ - ተሾመ አሰግድ

(አቤል ገ/ኪዳን)

ሙዚቃዎቹ የብዙዎች የፍቅር ታሪክ ውስጥ ቦታ አላቸው። ድምጹ ነጎድጓዳዊ ነው። ድምጻዊ ብቻ ሳይሆን የሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋችም ነው። ራሱ ኪቦርድ እየተጫወተ ከመዝፈኑ ባለፈም የሌሎችንም ሙዚቃዎች ሰርቷል። ላለፉት 32 አመታት ኑሮውን በአገረ አሜሪካ ቢያደርግም ዛሬም ድረስ በብዙዎች ልብ ውስጥ የታተሙ በወጣት ድምጻውያንም በብዛት የሚቀነቀኑ ሙዚቃዎች ባለቤቱ ተሾመ አሰግድ የዛሬው ገፃችን ትኩረት ነው።



የተወለደው በእለተ እንቁጣጣሽ መስከረም 1 ቀን 1945 ዓ.ም በያኔው ወለጋ ጠቅላይ ግዛት ቄለም አውራጃ ደምቢ ዶሎ ከተማ ውስጥ ነው። ስድስት ወንድ እና ስምንት ሴት በተወለደበት ቤተሰብ ውስጥ ተሾመ ለአቶ አሰግድ ይመር አራተኛው ልጅ ነው። ያሳደጉት አክስቱ ወ/ሮ አማከለች በአካባቢያቸው የሚታወቁ ሴት ናቸው። ተሾመ ገና የ5 ወር ህጻን እያለ ነው የአይን ብርሃኑን ያጣው። ነገር ግን ምናልባትም በዚያ ወቅት ሳይሆን አይቀርም ጥበብ ወደ ተሾመ የመጣችው። ከጥበብም ሙዚቃ።

ተሾመ ገና ከልጅነቱ ሙዚቃ እንደሚወድ ይናገራል። በተለይም የክብር ዶክተር አርቲስት ጥላሁን ገሰሰ ድምጽ በተሾመ ልብ ውስጥ ታትሞ ቀርቷል። የሌላኛው አንጋፋ ድምጻዊ ፍሬው ሀይሉ አይናማዬ ነሽ አይናማዬ የተሰኘ ሙዚቃንም በጣም እንደሚወደው እና ከአፉ እንደማይጠፉ ይናገራል። በአካባቢያቸው የማይጠፉት ባለ መሰንቆ የኦሮምኛ አዝማሪዎችም የተሾመን ጆሮ ስለውታል። እናም እሱም እድሉን ባገኘ ቁጥር ያንጎራጉራል። ወ/ሮ አማከል ደግሞ ቤት ስራ ላይ ሲሆኑ ሬዲዮ ከፍተው ለተሾመ የሚወደውን ሙዚቃ የማዳመጥ እድሉን ያመቻቹለታል።

የ6 አመት ልጅ ሳለ አንድ ቀን ሰርግ ላይ ከበሮ እየተመታለት ሲዘፍን በወቅቱ በወለጋ አካባቢ ሚሽን የነበራቸው ኦሮምኛ ተናጋሪው ካናዳዊው የፕረስባይቴሪያን ሚሽን  አገልጋይ ካናዳዊው ሚስተር ረስል ይሰሙታል። ቀልባቸው ይወደዋል። ጠጋ ብለው ትምህርት ቤት መሄድ ትፈልጋለህ አሉት። ተሾመ ትምህርት ቤት ምን እንደሆነ ባያውቅም አዎ አለ። ይዘውት መኪናቸው ውስጥ ገቡ። ወ/ሮ አማከለች ተጠሩ። ልጅሽን ላስተምረው ልወስደው ነው አሏቸው። እሺ አሉ። ሚስተር ረስል ለተሾመ አዲስ ቁምጣ፤ ሸራ ጫማ እና ጥብቆ ሰጡት። ከልጆቹ ጋር እንግሊዝኛ ቋንቋን በቤቱ ሌላውን ትምህርት በሚሽኑ እያስተማረ ያሳድገው ጀመር። አዲስ ሕይወት ተጀመረ። ከትምህርቱ ጎን ለጎን ግን አዲስ አጋጣሚም ተፈጠረ። የሚስተር ረስል ባለቤት ኦርጋን ይጫወታሉ። በቤታቸው በእግር እየተረገጠ የሚጫወቱት አርሞኒየም የተባለ መሳሪያ አላቸው። ይህ ሙዚቃን ለሚወደው ተሾመ ፍጹም አስደሳች ሆነለት። ቀስ በቀስ እሱም መጫወትን መልመድ ያዘ።

ከእለታት አንድ ቀን ሚስተር ረስል ተሾመን ወደሚያስተምሩበት አሜሪካን ሚሽን አንድ ትልቅ እንግዳ መጣ። ለእንግዳው አቀባበል አበባ እንዲያበረክት የተመረጠው ደግሞ በእድሜ ትንሹ ተሾመ ነበር።አበባውን አበረከተ።እንግዳው ትንሹን ተሾመ አፉን ኦሮሞ ቤክታ ብለው ጠየቁት።ኦሮምኛ እንደሚችል በኦሮምኛ ነገራቸው። እኛ ማን ነን አሉት። የኢትዮጵያ ብርሃን ጃንሆይ ነዎት አላቸው። ምን ቢደረግለት እንደሚወድ ጠየቁት። ልጅ ነውና አዲስ ሸራ ጫማ እንዲገዙለት እንደሚፈልግ ነገራቸው። መሻቱ ተፈጸመለት። ጃንሆይ ወደ ሚስተር ረስል ዞሩ። ሚስተር ረስልም ትምህርት ቤቱ ከበጀት አንጻር ያለበትን ችግር አስረዱ። በትምህርት ቤቱ ከሚማሩ አይነ ስውራን ተማሪዎች ስምንቱ ወደ ሌላ ቦታ ሄደው እንዲማሩ ተወሰነ። አራቱ ወደ ባኮ አራቱ ወደ ሰበታ። ወደ ባኮ ከተዘዋወሩት አራት ተማሪዎች መሀከል አንዱ ተሾመ ሆነ።

ባኮ ለጥቂት አመታት ከቆየ በኋላ 1959 ሰበታ መርሀ እውራን ተቀላለቀለ። ወደ ሰበታ መምጣቱ ለተሾመ የሙዚቃ ሕይወት መሻሻል አስተዋጽኦ አደረገ። ትምህርት ቤቱ ብዙ የሙዚቃ መምህራን ነበሩት። የሙዚቃ ባንድም ነበረው። እንደ ጓደኛም እንደ አርአያም የሚያየውን አብዱቄ ከፈኔንም ተዋወቀ። ከባንዱ ጋር ሙዚቃውን መጫወት ቀጠለ። በወቅቱ ያሬድ የሙዚቃ ትምህርት ቤትን ለመቀላቀል ቢሞክርም ትምህርት ቤቱ አይነስውራንን ማስተማሪያ መላው ስለሌለው አልተቀበላቸውም ነበር። ቢሆንም ታዋቂው የሙዚቃ ቀማሪ አሸናፊ ከበደ በግላቸው እነ ተሾመን በሳምንት ሁለት ቀን እየወሰዱ ትምህርት ያስተምሯቸው ነበር። እነ ሲራክ ታደሰን 4ኛ ክፍል ጦርም እንዲሁ እነ ተሾመን ያግዙ ነበር። በየሁለት ሳምንቱ ወደ ሰበታ ጎራ የሚሉት አንድ ሁለት ጊዜ ሽልማት ያበረከቱለት ሲሆን ሙዚቃው ላይ እንዲበረታም ገፋፍተውታል።

ከሰበታ በኋላ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ወደ ኮከበ ጽባህ ተቀላቀለ። እዚያ ደግሞ  ጓደኛው አብዱቄ የወንዶች የሙዚቃ ቡድን አቋቋመ። ቀስተ ደመና የሚባል 7 አይነ ስውራን አንድ ላይ ሆነው ያቋቋሙት ባንድም ነበር። ይህ ባንድ ባቲ እና ትዝታ የተሰኘ አልበም የሰራ ሲሆን እዚህ ውስጥ ካሉት ሙዚቃዎች መሀከል አንዱ በክብር ዶክተር ጥላሁን ገሰሰ የተዘፈነው ይህች አጋጣሚ ሙዚቃ አንዱ ነው። ሙዚቃው ተሾመ ሊጫወተው ተብሎ የተዘጋጀ ሙዚቃ የነበረ ቢሆንም አሳታሚው ከተሾመ ይልቅ ለጥላሁን የተሻለ ይሆናል ተብሎ በመታመኑ ጥላሁን እንዲዘፍነው ተደርጓል። የሙዚቃውን ገቢ ጥላሁን ለኢትዮጵያ አይነ ስውራን ማህበር የሙዚቃ ቡድን ለግሷል።

የስርአት ለውጥ መጣ እና ጃንሆይ ወርደው ደርግ ስልጣኑን ያዘ። የእናት አገር ጥሪ መጣ እና እነ ተሾመም በሙዚቃቸው አገራዊ ግዴታቸውን ተወጡ። ደርግ ከምስራቅ ጀርመን ጋር ወዳጅ ነበርና የትምህርት እደል ተገኘ። የኢትዮጵያ አይነ ስውራን ማህበር የመጣውን የትምህርት እደል ለተሾመ ሰጠ። ወደ ምስራቅ ጀርመን ሄዱ የፒያኖ አጠቃቀም እና ጥገና ትምህርት ተማረ። ከምስራቅ ጀርመን ሲመለስ ሙዚቃን መጫወቱን ቀጠለ። ቪላቨርዴ የሚባል ቤት ከኩኩ ሰብስቤ ጋር ሙዚቃ መጫወት ቀጠለ። ከዚያም ዋቢ ሸበሌ እና ሂልተን ሆቴል ላይ ከኢትዮ ስታር ባንድ ጋር መጫወት ቀጠለ።

ቀጣዩ የተሾመ የሕይወት አቅጣጫ ከአገር የሚያስወጣ ሆነ። ወደ ጎረቤት አገር ጂቡቲ ተጓዘ። እዚያ ለ5 አመት ቆየ። እዚያ እያለ ነው ተወዳጅ የሆኑትን ስራዎቹን መስራት የጀመረው። ከሰራቸው ስራዎች አብዛኞቹ ሙዚቃዎች ዛሬም ድረስ በሕዝብ ጆሮ ላይ የታተሙ ናቸው። በተለይም የኔ አካል የኔ ነሽ እያደር እንደ አዲስ እየተደመጠ ያለ ሙዚቃው ነው።

**የኔ አካል የኔው ነሽ**
**ምን አወርስሻለሁ**
**አንጀትና ልቤን**
**ያው ትቼልሻለሁ**

ይህ ሙዚቃ ዛሬም አዲሱ ትውልድ እንደ አዲስ ይሰማዋል ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ድምጻውያን ተደግሞ ተዘፍኗል ፤ በሙዚቃ ተሰጥኦ ውድድሮች ላይ ብዙ ወጣቶች ባለ ተሰጥኦ መሆናቸው የሚያሳዩበት አልበም ነው። ሌላኛው እሱም ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠው እንዲያው ዘራፌዋም ተወዳጅ ስራው ነው። ደግሜ ስሰማው እንዴት እንደዚህ አድርጌ ዘፈንኩበት ብዬ የምደነቅበት ሙዚቃ ነው ይላል። ሕዝብ በጣም የሚወድለት ሌላኛው ስራው ደግሞ የኩባያ ወተት ነው። ከሮሃ ባንድ ጋር በአምባሰል ሙዚቃ ቤት የተዘጋጀው ይህ ሙዚቃው በወቅቱም ዛሬም ተወዳጅ ሙዚቃ ነው ብቻ ሳይሆን የተሾመ መታወቂያውም ነው ማለት ይችላል።

**የኩባያ ወተት**
**የሰውም አረፋ**
**በሽታዬን የሚያውቅ**
**አስታማሚ ጠፋ**

*ያንን ጋራ የተሰኘው ሙዚቃውም እንዲሁ ተወዳጅ ሙዚቃው ነው።*

**ያንን ጋራ አቋርጠሽ ሁሌ ማልምሽ**
**ያንን ጋራ አቋርጠሽ በአካል የማይሽ**
**የአገሬ ልጅ እንደምንድን ነሽ**

ካላጣሽው አካል ፤ ሞት አደላድሎን እና በእጆቼ እየዳሰስ ኩም በኤልያስ ጉሮሮ ሲደመጡ አዲስ ቀለም ያገኙ የሌሎች ዝነኛ ድምጻውያን ውብ ሙዚቃዎች ናቸው። ኤልያስ ከበርካታ አንጋፋ ድምጻውያን ጋር በጋራ በመሆን 2 አልበም ሰርቷል። አንደኛው አልበም ከበዛወርቅ አስፋው፤ ኤልያስ ተባበል እና ማርታ አሻጋሪ ጋር በመሆን የሰራው ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ከራሄል ዮሀንስ፤ አሰፉ ደባልቄ እና ኬኔዲ መንገሻ ጋር በመሆን የሰራው ነው። በተለይ ከራሄል ጋር የዘፈነው ገላዬ ናና እና በአምባው ላይ በጣም ተወዳጅ ሙዚቃዎች ናቸው።

ኤልያስ በግሉ ሶስት በጋራ ሁለት አልበሞችን ያወጣ ሲሆን ለሌሎችም ድምጻውያን ሙዚቃ ሰርቷል። ከኢትዮ ስታር ባንድ ጋር በመሆን በጋራ ያቀናበረው የቴዎድሮስ ታደሰ አልበም ሉባንጃዬ ለዚህ ተጠቃሽ ነው። የአልበሙ መጠሪያ የሆነው ሉባንጃዬ እና ቀን ሳይመሽ ሳይጨልም በጊዜ የተሾመ ስራዎች ናቸው። ከኦርኬስትራ ኢትዮጵያ ጋር በመሆን ያቀናበራቸው አልማዝን አይቼ እና ያለቀሰም ሲስቅ የሳቀም ያለቅሳልም እንዲሁ ተወዳጅ ስራዎቹ ናቸው። ተሾመ ድምጻዊ ብቻ አይደለም። ማሲንቆ አኮርዲዮን እና ኪቦርድን ጨምሮ ብዙ ስራዎችን ሰርቷል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የተሾመ ስራዎች ዛሬም ድረስ ተወዳጅ የመሆናቸውን ያህል የኮፒራይት ጥሰት ሰለባ ናቸው። ብዙዎች የሚያውቁት በድምጻዊ ጎሳዬ ቀለሙ (ጃኪ ጎሳዬ) የተዘፈነው የተሾመ ተወዳጅ ስራ የኔ አካል አንዱ ሲሆን ድምጻዊው ተሾመን ይቅርታ ጠይቆ ችግሩ ተፈቷል። ከዚህ ሙዚቃው በተጨማሪ ሌሎቹም ስራዎቹ እንዲሁ በድጋሚ የተዘፈኑ ሲሆን ተሾመ በዚህ ዙሪያ በተደጋጋሚ በሚያሰማው ቅሬታ ወጣት ድምጻውያን ከመዝፈናቸው በፊት የሙዚቃውን ባለቤቶች ፈቃድ መጠየቅ አለባቸው ብሏል። ከዚህ ቀደም እሱም የሌሎችን መዝፈኑን ነገር ግን ይህን ሲያደርግ ባለቤቶቹን እንዳስፈቀደ የሚናገረው አንጋፋው ድምጻዊ በኮፒ ራይት መብት ዙሪያ መሰራት እንዳለበት በአጽንኦት ተናግሯል።

ተሾመ በአሁኑ ወቅት በአሜሪካ አገር የሚኖር ሲሆን በአንድ ወቅት በሰጠው ቃለመጠይቅ ናዮሚ ተሾመ የምትባል በሙያዋ የህክምና ዶክተር የሆነች እና አዲስ አበባ የምትኖር ልጅ እንዳለችው ተናግሯል።




# የህዳሴ ግድብ በህፃናት አንደበት

**አስናቀ ፀጋዬ**

በዘንድሮው ዓመት ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የህፃናት አስተዋፅኦ ጎልቶ ታይቷል። ህፃናቱ በተለይ የልደት በዓላቸውን ወጪ ጭምር በመተው ቦንድ እንዲገዛላቸው በማድረግና የልደት በዓል ስጦታቸውንና የኪካቸውን ወጪ ጨክነው ለግድቡ በማበርከት የራሳቸውን አሻራ አሳርፈዋል።


ህፃን ክርስቲያን ሰለሞን አዲስ አበባ በሚገኘው ይርጋለም አካዳሚ የአንደኛ ክፍል ተማሪ ናት። ‹‹የህዳሴ ግድብ ለእኔ መብራት የሚሰጠኝ ነው›› ትላለች። የህዳሴ ግድብ ተጠናቆ መብራት እንዲያመነጭ ታዲያ ጠንክራ እየተማረች እንደምትገኝና ለግድቡም የራሷን አስተዋጽኦ እያበረከተች እንደምትገኝ ትገልፃለች። ከእናቷ ተቀብላ ያጠራቀመቻቸውን ገንዘብ ለህዳሴ ግድብ ግንባታ እንዳበረከተችም ትናገራለች። በእርሷ እድሜ ያሉ ህፃናትም ወላጆቻውን ጠይቀው ገንዘብ በማጠራቀም ለገድቡ ግንባታ ያበርክቱም ትላለች።

ህፃን ምዕራፍ ወልደሩፋኤል በቅዱስ ማርቆስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የሶስተኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን ‹‹የህዳሴ ግድብ ለእኔ የህልውናዬ መሰረት ነው›› ይላል። የህዳሴ ግድብ ሲጠናቀቅ ያለመብራት ቁጭ ብለው እራት የሚበሉትንና የሚያጠኑትን ህፃናት ወደ ብርሃን እንደሚያመጣቸውና በቴክኖሎጂም ጭምር ታግዘው እንዲኖሩ እንደሚያስችላቸው ይገልፃል።

ከወላጆቹ ተቀብሎ ገንዘብ በማጠራቀምና ቦንድ በመግዛት ለህዳሴ ግድብ ግንባታ ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝም ይናገራል። በትምህር ቤት በሚዘጋጁ የድጋፍ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች ላይ በመሳተፍና ቅስቀሳ በማድረግ ድጋፍ እያደረገ እንዳለም ይገልፃል። በቀጣይም ለግድቡ የሚያደርገውን ድጋፍ እንደሚቀጥልና ሌሎች ህፃናትም ለግድቡ ድጋፍ እንዲያደርጉ ቅስቀሳ እንደሚያደርግ ይጠቁማል።

በአርዲ ዩዝ አካዳሚ የሶስተኛ ክፍል ተማሪ የሆነው ህፃን ዮሚዩ ሰለሞን በበኩሉ ‹‹ታላቁ የህዳሴ ግድብ ለእኔ የመብራት ምንጭ›› ነው ይላል። ልክ እንደ ህፃን ክርስቲያንና ህፃን ምእራፍ ሁሉ ከወላጆቹ ገንዘብ በመጠየቅና በማጠራቀም ለግድቡ ግንባታ እያበረከተ እንደሚገኝ ይገልፃል።

ሌሎች በእርሱ እድሜ ክልል የሚገኙ ህፃናትም ወላጆቻቸውን በመጠየቅና ቦንድ እንዲገዙላቸው በማድረግ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ድጋፍ ማድረግ እንዳለባቸውም መልእክቱን ያስተላልፋል።



የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ ብሔራዊ ምክር ቤት ፅህፈት ቤት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ፍቅርተ ታምር እንደሚሉት ባለፉት ስድስትና ሰባት አመታት ህፃናት ለግድቡ ግንባታ ድጋፍ እንዲያደርጉ በርካታ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል። ይህ ስራ በክልሎችም ሰፍቶ እየተከናወነ ይገኛል። የ11ኛ አመት የግድቡ በዓልም ‹‹ግድባችን የአንድነታችን ብርሃን ነው›› በሚል መሪ ቃልም በሁሉም ክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮችና በመላው ኢትዮጵያ ሲከበር ሰንብቷል።

በህፃናት ላይ አተኩሮ መስራት ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያትም ህፃናት የነገ አገር ተረካቢ በመሆናቸውና ወላጆቻቸው አሻራቸውን ያሳረፉበትን ግድብ ተረክበው ወደፊት እንዲያስቀጥሉ ነው። በተለይ ህፃናት ለግድቡ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ድጋፍ እንዲኖራቸውም ስለሚያስፈልግ በግድቡ ዙሪያ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ውይይት እንዲያደርጉ፣ በትምህርት ቤት እንዲከራከሩ፣ ግጥም እንዲያቀርቡና የመሳሰሉትን እንዲያደርጉ የሚያስችሉ መድረኮች እየተዘጋጁ ይገኛሉ። በቀጣይም ይኸው መድረክ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። በህፃናት መካከል የሥዕል፣ፊልም፣ ግጥምና ሌሎችም ውድድሮች ይካሄዳሉ።

ከዚህ ባለፈ በዘንድሮው በጀት አመት በተለየ መልኩ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የሚገኙ ህፃናትና ታዳጊዎች ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ በርካታ ድጋፎችን አድርገዋል። የልደታቸውን ወጪ፣ ቤተሰቦቻቸው ቦንድ እንዲገዙላቸው በማድረግ ድጋፋቸውን አሳይተዋል። አሁን ደግሞ በቦንድ ሳምንት በአገር አቀፍ ደረጃ በየትምህርት ቤቱ ተማሪዎች በቦንድ ግዢ እየተሳተፉ ይገኛሉ። በዚህም በርካታ ገንዘብ መሰብሰብ ተችሏል። በቀጣይም ‹‹አሻራዬን አኑሪያለሁ›› የሚል የደረት ፒን ሁሉም ወላጆች ለልጆቻቸው እንዲገዙና ለልጆቻቸው ስጦታ እንዲሰጡ የማድረግ ፕሮግራም ይካሄዳል።

# ስፖርት

## አራት የቻምፒዮንስ ሊግ ዋንጫዎችን በሶስት ክለቦች

**ብርሃን ፈይሳ**

የአውሮፓ ቻምፒዮንስ ሊግ ክብርን በተደጋጋሚ በመጎናጸፍ እንደርሱ የደመቀ ተጫዋች የለም። እርሱ ተጫዋች በነበረበት ዘመን ከዓለም ምርጥ የመሃል ሜዳ ተጫዋቾች መካከል ተጠቃሽ ሲሆን፤ ታላቁ ብራዚላዊ የእግር ኳስ ሊቅ ፔሌ ከፊፋ ምርጥ ተጫዋቾች መካከል አንዱ መሆኑን ድምጹን በመስጠት አስመስክሮለታል። ለአገሩ ብሄራዊ ቡድን ተሰላፊ ሆኖ በርካታ ታሪኮችን ከማጻፍ በዘለለ ከሆላንድ፣ ስፔን፣ ጣሊያን እና ብራዚል ክለቦች ጋር በተጫዋችነት ስኬታማ ጊዜያትን አሳልፏል። ጫማውን ከሰቀለ በኋላም ወደ አሰልጣኝነቱ ጎራ በማለት የጣሊያን፣ የቻይና፣ የስፔን እና ካሜሮን ክለቦችን መርቷል። በሆላንድ ብሔራዊ የእግር ኳስ ቡድን ታሪክ ምርጥ ተጫዋቾች መካከል አንዱ የሆነው ክላረንስ ሴዶርፍ ዛሬ መዳረሻውን አዲስ አበባ ላይ አድርጓል።

ሴዶርፍ እአአ 1976 እግር ኳስን የሙጥኝ ባለ ቤተሰብ ውስጥ ተወለደ፤ ሁለቱ ታላላቅ ወንድሞቹ እግር ኳስን ሲያዘወትሩ አባታቸው ጆን ሴዶርፍም የቀድሞ ተጫዋች ነበሩ። ይህም ትንሹን ሴዶርፍ ወደ እግር ኳስ ያስገባው ሲሆን፤ በ6 ዓመቱ በሚኖርበት አካባቢ የሚገኘውን የእግር ኳስ ማሰልጠኛ ማዕከል ተቀላቅሏል። ከቆይታ በኋላም እንደወንድሞቹ ሁሉ እርሱም የአያክስ ወጣቶች አካዳሚን በመቀላቀል በስልጠና ላይ ቆይቶ እአአ በ1992 የመጀመሪያ ጨዋታውን አካሄደ። በወቅቱ የክለቡ ትንሹ ተጫዋች እርሱ ይሁን እንጂ በአሰልጣኙ ዘንድ ቀዳሚ




ተመራጭ ለመሆን ጊዜ አልፈጀበትም።

የክለቡ ቁልፍ የመሃል ሜዳ ተጫዋች በመሆን በቆየባቸው ዓመታትም ከክለቡ ጋር በርካታ ስኬቶችን ማስመዝገብ ችሏል። ከእነዚህ መካከል በ35ኛው ደቂቃ ተቀይሮ በመግባት ለክለቡ ባበረከተው አስተዋጽኦ የጣሊያኑን ኤሲሚላንን በመርታት እአአ የ1995 የአውሮፓ ቻምፒዮንስ ሊግ ዋንጫን ማንሳቱ ተጫዋቹ በክለቦች ዓይን እንዲገባና የምርጥ ተጫዋችነት ሕይወቱ ይበልጥ እንዲያብብ ምክንያት ሆኗል። በቀጣዩ ዓመት የሴሪኤ ውን ክለብ ሳምፕዶሪያን ቢቀላቀልም ቆይታው ግን ከአንድ ዓመት የዘለለ ሊሆን አልቻለም።

በመሆኑም ክለቡን ከተሰናበተ በኋላ ወደ ስፔን በመሻገር በሪያል ማድሪድ ማሊያ በላሊጋው ታየ፤ በመጀመሪያው ዓመት ቆይታውም የላሊጋውን ዋንጫ ከክለቡ ጋር በመሆን ለማንሳት ችሏል። በነጫጮቹ ቤት በነበረው የሶስት ዓመታት ቆይታ በጥቅሉ አራት ዋንጫዎችን ሲያነሳ፤ እአአ 1998 ያሳካው የአውሮፓ ቻምፒዮንስ ሊግ ዋንጫን ነበር። ተጫዋቹ ከሁለት ክለቦች ጋር ትልቁን ዋንጫ በማስመዝገብ ስኬቱን ማጣጣም ችሏል። እአአ የ1999/2000 የውድድር ዓመትም ከክለቡ ጋር በመለያየት ፊቱን ዳግም ወደ ጣሊያን በማማተር፤ በ23 ሚሊዮን ዩሮ የኢንተር ሚላን ንብረት ለመሆን ቻለ። ከሁለት ዓመታት ቆይታ በኋላ ግን ሌላኛው የጣሊያን ክለብ የኤሲሚላን ተጫዋች ሆነ።

በቀጣዩ ዓመትም ለክለቡ ከ26 ዓመታት በኋላ የመጀመሪያ የሆነውን የኮፓ ጣሊያን ዋንጫ በማንሳት የታሪኩ አካል ለመሆን በቃ። በእግር ኳስ ሕይወቱ የተሻለ ጊዜን ባሳለፈበት ክለብ በዚያው ዓመት የአውሮፓ ቻምፒዮንስ ሊግ ዋንጫን የክለቡ ንብረት ለማድረግ በቃ። ይኸውም ተጫዋቹ በሶስተኛ ክለቡ ያገኘው የቻምፒዮንስ ሊግ ዋንጫ ሲሆን፤ በታሪክ ብቸኛው ተጫዋች እንዲባልም ምክንያት ሆነው። ቀጣዩን ዓመትም የሴሪኤውን ዋንጫ በማንሳት ስኬቱን ቀጥሎ ከአራት ዓመት በኋላ በእግር ኳስ ታሪኩ አራተኛውን የአውሮፓ ቻምፒዮስ ሊግ ዋንጫ ከክለቡ ጋር አነሳ። በዚህ ወቅት የእርሱ ሚና እጅግ ከፍተኛ ሲሆን፤ በዚያው ዓመት የሱፐርካፕ ዋንጫን በማንሳት በክብር ላይ ክብርን ለመጎናጸፍ ቻለ። ይኸውም በፊፋ እና በአውሮፓ እግር ኳስ ማህበር ምርጥ ተጫዋችነት ምርጫ ውስጥ በመካተት የወቅቱ ምርጥ የመሃል ተጫዋች ተሰኘ።

በኤሲሚላን ቤት ለአስር ዓመታት ቆይታ ያደረገው ክላረንስ ሴዶርፍ በእግር ኳስ ሕይወቱ ይበልጥ የሚታወቀው በቻምፒዮንስ ሊግ ስኬቱ ነው። እአአ 2012 የአውሮፓ ቻምፒዮንስ ሊግ 20ኛ ዓመቱን ባከበረበት ወቅትም ምርጥ በሚል በደረጃ ካስቀመጣቸው 20 ተጫዋቾች መካከል ሴዶርፍ ሰባተኛ ላይ ይገኛል። ይህንን ተከትሎም የዘንድሮው የአውሮፓ ቻምፒዮንስ ሊግ ዋንጫ ጉብኝት በተጫዋቹ ይታጀባል። ዋንጫው መዳረሻ ካደረጋቸው ጥቂት የአፍሪካ ከተሞች መካከል አንዷ የሆነችው አዲስ አበባም ዛሬ እንግዳዋን ትቀበላለች።